1642

# መጽሐፈ ፡ ጨዋታ ፡
# ሥጋዊ ፡ ወመንፈሳዊ ።

በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡
ከዘነበ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተጻፈ ።

በገሀ ፡ ጽባሕ ፡ ማተሚያ ፡ ታተመ ፡
፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዲስ ፡ አበባ ።

www.ethiopianorthodox.org

## መጽሐፈ ፡ ጨዋታ ፡ ሥጋዊ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

እግዚአብሔር ፡ እስቲሸር ፡ ሚካኤል ፡ እስቲሞት ፡ ምነው ፡ በኖርሁኝ ። ገብርኤል ፡ ሲያንቀላፉ ፤ ሩፋኤል ፡ ሲዶክም ፤ ሐሰተኛው ፡ ዲያብሎስ ፡ ንስሐ ፡ ይገባል ።

ክረምት ፡ ሲመጣ ፡ ሰማይ ፡ እንዲከብድ ፤ የጠሉትም ፡ ሰው ፡ ሲመጣ ፡ እንደዚያ ፡ ይከብዳል ። ዘወትር ፡ ከሚያጋድል ፡ አህያ ፡ ተሸክሞ ፡ መሄድ ፡ ይሻላል ። ከማያስተካክል ፡ መላክተኛ ፤ የማለዳ ፡ ወፍ ፡ ትሻላለች ፤ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ንጋቱን ፡ ትነግራለችና ።

ደንጋይና ፡ ጭቃ ፡ ቢቀባበሉ ፡ ታላቅ ፡ ቤት ፡ ረጅም ፡ ቅጥር ፡ ይሆናሉ ፤ እናንተም ፡ መሬታውያን ፡ ሰዎች ፡ እንደዚህ ፡ ብትረዳዱ ፡ ጥበባችሁና ፡ ኃይላችሁ ፡ ከሰማይ ፡ በደረሰ ።

ኮሶና ፡ ክረምት ፡ ሬት ፡ ይመራል ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። ድሬ ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ ገንዘብን ፡ ለመቆራኘት ፡ የተሠራ ፡ ሰንሰለት ፡ ነው ። እሬት ፡ መብላት ፡ ቢለመድ ፡ ባልተለቀቀም ፡ ነበር ፤ ዝሙትም ፡ ላለመደው ፡ ሰው ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።

ጣዝማ ፡ እጅግ ፡ ብልህ ፡ ናት ፤ መሬት ፡ ቀዳ ፡ ገብታ ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ መድኃኒት ፡ የሚሆን ፡ ማር ፡ ትሠራለች ። ምነው ፡ እናንተ ፡ ሰዎች ፡ ወይ ፡ ከፈጣሪ ፤ ወይም ፡ ከሰው ፡ ብልሀትን ፡ አትፈልጉምን ።

የምሥራች ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ልብ በደስታ ፡ ባሕር ፡ ይሰጥማል ። እርጎን ፡ ከፍቶ ፡ ቢተውት ዝንብና ፡ ድመት ፡ ይጫወትበታል ፤ አገርንም ፡ አቅንቶ ፤ ሰው ፡ ካላስቀመጠበት ፡ ተመልሶ ፡ ዱር ፡ ይሆናል ።

ባበቱ ፡ የሚከረ ፡ ሰው ፡ ጅል ፡ ነው ። የሰው ፡ አበቱ ፡ አንድ ፡ አዳም ፡ አይደለምን ። ሴትን ፡ ወንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይደርስባታል ፡ መንታ ፡ ትወልዳለች ፡ እህልም ፡ አንዲት ፡ ፍሬ ፡ ተዘርታ ፡ ብዙ ፡ ታፈራለች ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ክቶ ፡ አንዴት ፡ ነው ፤ እንጃ ፡ ማን ፡ ያውቀዋል ፡ ያ ፡ የጠቢቦች ፡ ጠቢብ ፡ ያውቀው ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጃ ።

ፈረስ ፡ በብረት ፡ ልጓም ፡ ይገታል ፡ የሕዝብም ፡ ልጓሙ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ መቃብር ፡ መልክም ፡ ጉድጓድ ፡ ነው ፡ ብስሉንና ፡ ጥሬውን ፡ ይከታልና ። ወዳጅ ፡ ቢወዱት ፡ ይወዳል ፤ መሬትም ፡ ቢበሉት ፡ ይበላል ።

በርበሬ ፡ ላይን ፡ ቀይ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ፤ ምነው ፡ ቢሉ ፡ በብልሐት ፡ ገብቶ ፡ ሊለበልብ ። ክፉ ፡ ሰውም ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡ ኋላ ፡ ነገሩን ፡ ያመጣል ።

ቸር ፡ ሰው ፡ ለወዳጁ ፡ ጠጅ ፡ ነው ፤ ፍቅሩ ፡ ያሰክራልና ። ዝናም ፡ ከዘነመ ፡ በኋላ ፤ ቡቃያ ፡ ያበቅላል ፤ ንጉሥም ፡ ከወደደ ፡ በኋላ ፡ ይሾማል ።

ሽክላ ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ ወሀ ፡ አርሶ ፡ አሠርቶት ፡ መከታ ፡ እየሆነ ፡ እሳትን ፡ ያስወጋዋል ። ክፉም ፡ ሰው ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። ወንፊት ፡ ዱቄቱን ፡ እንዲነፋ ፤ ዘርዛራም ፡ ሸማ ፡ ጠጅን ፡ እንዲያወርድ ፤ ባለቤቱም ፡ ያልቻለውን ፡ ምሥጢር ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ አይችለውም ።

ቅቤ ፡ ከይብና ፡ ከጎት ፡ እንዲለይ ፤ በላይም ፡ እንዲሆን ፡ ጻድቅም ፡ ሰው ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

---

## ክፍል ፡ ፪ ።

ደመና ፡ ሰማይን ፡ እንዲሸፍነው ፤ ንጉሥም ፡ በሠራዊቱ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። ሳማና ፡ አብላሊት ፡ ለምለም ፡ መ



ስለው ፡ እንዲለበልቡ ፤ መናፍቃንም ፡ ሲቀርቧቸው ፡ እንደዚያ ፡ ናቸው ።

በቀስታና ፡ በዝግታ ፡ የተበጀ ፡ መዘወር ፡ ኋላ ፡ ጉልበት ፡ ይሆናል ። ወረቀት ፡ መልክም ፡ እርሻ ፡ ነው ፤ ብዙ ፡ ነገር ፡ ይዘራልና ። ጐታም ፡ አይሻ ፤ እርሱ ፡ ከቶት ፡ ይኖራልና ።

ማር ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ያገለግላል ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መጠጥ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መብራት ፡ ሆኖ ። ምነው ፡ ቢሉ ፡ የብልሕ ፡ ሥራ ፡ ነውና ፡ አሰርም ፡ የለው ።

ሕዝብና ፡ ሕዝብ ፡ ደጋና ፡ ቆላ ፡ ናቸው ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ ገበያ ፡ ነው ፤ ሁሉን ፡ ያገናኛልና ። ሽክላ ፡ ከተሰበረ ፡ በኋላ ፡ ገል ፡ ነው ። መኳንንትም ፡ ከተሻሩ ፡ በኋላ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ።

ክፉ ፡ ሰው ፡ ሽንቱን ፡ በሸነ ፡ ጊዜ ፡ ኋላ ፡ ጉንፉን ፡ ይሆናል ፤ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ግብሩ ፡ ተጉድፍ ፡ የተወሐደ ፡ ነውና ፡ ማርና ፡ እሬትን ፡ ቢመዝኑ ፤ ማን ፡ ይደፋል ፡ እሬት ፤ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ክፉ ፡ መራራ ፡ ነውና ።

ከብዙ ፡ ቀን ፡ ደስታ ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ መከራ ፡ ይበልጣል ። ንጉሥ ፡ ምሰሶ ፡ ነው ፤ ሠራዊት ፡ ግድግዳ ፡ ናቸው ። መኳንንት ፡ ግን ፡ ማገር ፡ ናቸው ፤ ለንቋጣ ፡ ልጡ ፡ እንዲማልግ ፡ እንጨቱም ፡ ቀለል ፡ እንደሆነ ፤ ወስላታም ፡ ወዳጅ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

ጨጨው ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ይዘራል ፤ ምናልባት ፡ ሰልችተው ፡ ይተውኛል ፡ ብሎ ፡ ነውን ፤ ከሬት ፡ ጋራ ፡ ይጋባ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጃ ፡ የሚለቀው ፡ የለም ።

አንድ ፡ ዓይንና ፡ አንድ ፡ ዓይን ፡ ያላቸው ፡ ተጋብተው ፤ ሁለት ፡ ዓይን ፡ ያለው ፡ ልጅ ፡ ወለዱ ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ አንዱ ፡ ካባቱ ፡ አንዱ ፡ ከናቱ ፡ ነዋ ። የዚህ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዓለም ፡ ትርፉ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ መብላት ፡ መጠጣት ፡ ግ
ጋብና ፡ ኩራት ፡ ነው ። ኩራት ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ እንደርሱ ፡
ሆኖ ፡ የተፈጠረውን ፡ ሰው ፡ መናቅ ፡ ነው ።

ሰው ፡ ፍሪዳን ፡ አብልቶ ፡ አብልቶ ፡ ያሰባዋል ፡ በ
መጨረሻውም ፡ ይበላዋል ። ምነው ፡ ቢሉ ፡ አብልቶ ፡ መ
ብላት ፡ እንጂ ፡ ግብያ ፡ ነው ። ወርቅ ፡ ቢያብረቀርቅ ፡ ብር ፡
ያብለጨልጫል ፡ ምነው ፡ እናንተ ፡ መናናቃን ፡ ጥቂት ፡
ጥቂት ፡ ብልሐት ፡ አታውጡምን ።

የገንዘብ ፡ ብልሐት ፡ ምንድር ፡ ነው ። ሌላው ፡ የሠ
ራውን ፡ መብላት ፡ ነው ፤ ሰነፎች ፡ ሰዎችም ፡ እንደዚሁ ፡
ሌላ ፡ ሰው ፡ የሠራውን ፡ መብላት ፡ ይወዳሉ ።

ደሀ ፡ ከመሆን ፡ ሀብታም ፡ መሆን ፡ ይሻላል ፡ ምነው ፡
ቢሉ ፡ አይቸግርምና ። በምድር ፡ ከመኖር ፡ በሰማይ ፡ መ
ኖር ፡ ይሻላል ፤ ምነው ፡ ቢሉ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ መከራው ፡
ብዙ ፡ ነውና ።

ከባለጌ ፡ ፍቅር ፡ የንጉሥ ፡ ቁጣ ፡ ይሻላል ፤ የረሀብ ፡
ጌትነቱ ፡ መቼ ፡ ነው ፤ እኩል ፡ ቢታጣ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ ምነው ፡
ቢሉ ፡ የሌለውን ፡ አምጡ ፡ ይላልና ። የማጣትስ ፡ ጌትነቱ ፡
መቼ ፡ ነው ፤ የፈለጉት ፡ ነገር ፡ በታጣ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የጥጋብስ ፡
ጌትነቱ ፡ መቼ ፡ ነው ፤ መብልና ፡ መጠጥ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡
ነው ። የመብላትስ ፡ ትርፉ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ጥጋብ ፡ ነው ።

---

## ክፍል ፡ ፫ ።

ከልጋ ፡ ላይ ፡ ከምትውል ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ገጣብ ፡ አ
ህያ ፡ ይሻላል ፤ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ጭኖ ፡ ያበላልና ።

ጉጠት ፡ የበረደውንና ፡ የጋለውን ፡ ብረት ፡ እንዲይዝ ፤
እብድ ፡ ሰውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። መቃጥንና ፡ ብልህ ፡



መላክተኛ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ምነው ፡ ቢሉ ፤ ደኅና ፡ መስ
ለው ፡ ስበው ፡ ያስገድላሉና ።

እንስሶች ፡ ሁሉ ፡ የሚበሉት ፡ አንድ ፡ ሣር ፡ ነው ፤ ም
ነው ፡ ፋንድያቸው ፡ ተለዋወጠ ። ሰዎችም ፡ አባታቸው ፡
አንድ ፡ አዳም ፡ ሲሆን ፡ ምነው ፡ አይነታቸው ፡ በዛ ።

ንጉሥ ፡ የቃጣውን ፡ ጽዋ ፡ በጠጣህ ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀ
ቅ ፤ ሌሊት ፡ እንዳያንገዝዝህ ። አቀፈ ፤ አዘለ ፡ ማለት ፡ ምን
ድር ፡ ነው ፤ ስሙና ፡ አጠራሩ ፡ በየራሱ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እ
ንጂ ፡ ሁሉም ፡ ተሸከመ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሰይጣን ፤ ጋኔን ፤ ዛር ፤ ማለት ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ ስሙ ፡
መለዋወጡ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ጋኔን ፡ ነው ።

የውሻ ፡ ጅራቱ ፡ ወደላይ ፡ እንዲቆም ፤ የሹመት ፡ ፈላጊም ፡
ልብ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። መርፌ ፡ ሸማን ፡ የሚወጋው ፡ ምን ፡
አጠቀም ፡ ብሎ ፡ ነው ፤ በኋላው ፡ እንጂ ፡ ፈትል ፡ ተከት
ሎታል ፤ እንዚያ ፡ እንዲጠቃቀሙ ፡ አያውቁምን ፤ እንደዚ
ሀ ፡ ያለ ፡ ሞኝ ፡ የፊቱን ፡ እንጂ ፡ የኋላውን ፡ የማያይ ፤ ይ
ልቁንስ ፡ የርሱን ፡ ቀዳዳ ፡ በጠቀመ ።

ውሽማ ፡ በሴት ፡ ዘንድ ፡ ማር ፡ ነው ፤ ባል ፡ ግን ፡ ሬት ፡
ነው ፤ ስለዚህ ፡ የስስት ፡ መልክና ፡ የሴት ፡ ልብ ፡ አንድ ፡
ነው ፤ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ወዲያው ፡ ይለዋወጣልና ።

ብር ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ኃጢአት ፡ ውሎ ፡ ይሆን ፡ ሲሸጥ ፡
ሲሸጥ ፡ ኖሮ ፡ ከእሳት ፡ የሚገባ ፤ ለካ ፡ አታውቅምን ፤ ሰውን ፡
ሁሉ ፡ እንጂ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሲአደርግ ፡ ከነሮቤል ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ይሁዳ ፡ ይኖራል ፤ እርሱ ፡ እሳት ፡ ያልገባ ፡ ማን ፡
ይግባለት ።

አገር ፡ ከየር ፡ ሲርቅ ፡ ቆላ ፡ ይሆናል ፤ ከየር ፡ ቢቀርብ ፡
ግን ፡ ደጋ ፡ ስለሆነ ፡ ውርጭ ፡ በረዶ ፡ ይሆናል ፤ እንደዚሁ
ም ፡ ከንጉሥ ፡ የቀረበ ፡ ልምላሜ ፡ ያገኛል ፤ ከንጉሥ ፡ የራ

www.ethiopianorthodox.org

ቀ ፡ ግን ፡ ደሀ ፡ ይሆናል ። አሳትንና ፡ ንጉሥን ፡ እጅግ ፡ አት ራቅ ፡ እንዳይበርድህ ፤ እጅግም ፡ አትቅረብ ፡ እንዳይፈጅህ ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

ከገንዘብ ፡ መልካም ፡ ማነው ፤ ወርቅ ፡ ነገርንና ፡ ጥልን ፡ የሚያስቀር ፡ ማነው ፤ ዕርቅ ፤ ጉዋሪስ ፡ ማነው ፤ ጾድቅ ፡ ሣቅ ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ የደስታ ፡ ሳንቃ ፡ ነው ፤ ዘፈን ፡ ምን ድር ፡ ነው ፤ የደስታ ፡ ማለፊያ ፡ ነው ፤ እልልታ ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ የደስታ ፡ መከፈያ ፡ አዋጅ ፡ ነው ።

ልቅሶ ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ የኀዘን ፡ ወንገዝ ፡ ነው ። ትካዜ ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ የመከፋት ፡ ኀዝ ፡ ነው ።

እስስት ፡ ስትገላበጥ ፡ እንደምትጠላ ፤ ሁልጊዜም ፡ የ ሚለምን ፡ ሰው ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። ባለጌ ፡ በበቅሎ ፡ ላይ ፡ ቢሄድ ፤ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የወጣ ፡ ይመስለዋል ። ተኩላ ፡ ባሪያ ፡ ወደል ፡ ውሻ ፡ ይሻላል ፤ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ጌታውን ፡ በዬ ጊዜ ፡ ድራቱን ፡ ይቆላልና ።

ተጌጥ ፡ መልካም ፡ ማነው ፤ ወርቅና ፡ ብር ። ለሰልፍስ ፡ መልካም ፡ ማነው ፤ በሩድና ፡ አረር ። ተገላጋይ ፡ መልካም ፡ ማነው ፤ አስቀድሞ ፡ ማፈር ፤ ከሙብልስ ፡ ማፍጊ ፡ ማነው ፤ ማርና ፡ ሱካር ፤ ሰብሳቢስ ፡ ማነው ፤ መቃብር ።

ለሰውስ ፡ መልካም ፡ ማነው ፤ አገር ፤ ለወገብስ ፡ መልካም ፡ ማነው ፡ ዝናር ። ቀዝቃዛስ ፡ ማነው ፡ በረዶ ። ድንገተኛ ፡ ማነው ፤ አግኝቶ ፡ ማጣት ፡ ተንቆ ፡ መኖር ። ውርጭስ ፡ ማነው ፡ ሲበሉ ፡ ማየት ። መቃረዝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ ተሹሞ ፡ መሻር ። ብርድ ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ የቅናት ፡ ነገር ። የልብስ ፡ ዘርፍ ፡ ማነው ፤ ጭፍራ ። ከተራ ፡ ማን ፡ ይውላል ፤ ንጉሥና ፡ መ ነጽር ። ካረህ ፡ ማን ፡ ይውላል ፤ ነፍጠኛ ። ከሜዳ ፡ ማን ፡ ይውላል ፤ ፈረሰኛ ።



ደመና ፡ ብልሕ ፡ ነው ፤ ወሀን ፡ ከምድር ፡ አውጥቶ ፡ ምድርን ፡ ያጠጣልና ። ምነው ፡ ነገሥታትስ ፡ የደኃውን ፡ ለ ቆላ ፤ የቆላውን ፡ ለደጋ ፡ አያደርጉትምን ። የፍየል ፡ ንጉሥ ፡ ነምር ፡ ነው ፤ የበግ ፡ ንጉሥ ፡ ተኵላ ፡ ነው ። ያህያ ፡ ንጉሥ ፡ ጅብ ፡ ነው ። ያራዊት ፡ ንጉሥ ፡ አንበሳ ፡ ነው ። የክፋት ፡ ምንጭ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ።

እባብ ፡ የሰይጣን ፡ በቅሎ ፡ ናት ፡ ፋደት ፡ ውሻ ፡ በ መጣበት ፡ ጊዜ ፡ ትፈሳበታለች ። ተመልሶ ፡ እየጮኸ ፡ ይ ሸሻል ፤ ያም ፡ ስፍራ ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እየገማ ፤ ይኖራል ። ጻድቃንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ሊያስተ ምሩ ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በመካ ከላቸው ፡ አምጥቶ ፡ እንደውሻው ፡ ያባርራቸዋል ።

ንጉሥ ፡ ክርዩ ፡ የደኃውን ፡ ጩኸት ፡ ባይሰማ ፤ እ ግዚአብሔር ፡ መንግሥቱን ፡ ለተናቀ ፡ ሰው ፡ ይሰጥበታል ። መኰንን ፡ ቢከራ ፡ ይሞታል ፤ ወይም ፡ ይቃሠራል ። ዘመ ን ፡ ያነሣው ፡ ታላቅ ፡ ዜማ ፤ እንቅርት ፡ ያፈርጣል ።

ምላሰኛ ፡ ሴት ፡ ጡብ ፡ ከገረቤት ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ መላቧን ፡ መለመጥ ፡ ትጀምራለች ። ፍቅር ፡ ዘውድ ፡ ነው ። መልካም ፡ ጠባይ ፡ ዝናር ፡ ነው ። ትሕትናም ፡ ጫማ ፡ ነ ው ። ጥል ፡ ባሕር ፡ ነው ፤ ፍቅር ፡ ግን ፡ መርከብ ፡ ነው ። መልካም ፡ መላስ ፡ መልሐቅ ፡ ነው ።

ደመና ፡ በዘረ ፡ ጊዜ ፡ ጨው ፡ ይቀልጣል ፤ የሰው ፡ ኃጢአት ፡ በበዛች ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፡ ይርቃል ። የሰው ፡ ገንዘብ ፡ የለመደ ፡ ሹም ፤ ያህያ ፡ ሥጋ ፡ የለመደ ፡ ጅብ ፡ አይቻልም ። መጋዝ ፡ ቢከረከር ፡ ምሣር ፡ ይፈልጣል ። ምነው ፡ እናንተ ፡ ሰዎች ፡ እንዳቅ ም ፡ እንዳቅማችሁ ፡ ብልሐት ፡ አትፈልጉምን ። ነጋዴ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቢያረጅ ፡ ከገበያ ፡ ሄዶ ፡ ይጐለታል ፡ ሌባ ፡ ቢያረጅ ፡ ልብሱን ፡ ተገፎ ፡ ተአሊጋ ፡ ውስጥ ፡ ይሰወራል ።

አመድ ፡ የእንጨት ፡ ሬሳ ፡ ነው ፡ ማን ፡ ይቀብረዋል ፡ ነፋስ ። ዘወትር ፡ እየቀበረ ፡ ከሚጸልዩ ፡ ሰው ፡ ሲኖጋ ፡ የሚንጫጩ ፡ ወፎች ፡ ይሻላሉ ። መልክም ፡ ጠጅ ፡ በጠጡት ፡ ጊዜ ፡ እክል ፡ ሁሉ ፡ ብርሃን ፡ ይሆናል ። ስካር ፡ ምሽት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ጨለማ ፡ ይሆናል ።

ጥበብን ፡ ለምን ፡ ትፈልጓታላችሁ ፡ ከገበያ ፡ አትገዛ ፡ ከምድር ፡ አትበቅል ። ከኪሩቤል ፡ ጀርባ ፡ ካለው ፡ ከሕይወት ፡ ምንጭ ፡ በሃይማኖት ፡ በርጭቆ ፡ ቅዱ ።

በሬ ፡ በቅልጥሙ ፡ ቀበቱን ፡ ይዞት ፡ ይኖራል ፡ ገና ፡ ኋላ ፡ ለቁርበቱ ፡ ማልፊያ ፡ ይሆንኛል ፡ ብሎ ፡ ነውን ። የዱሮም ፡ ልጆች ፡ እንደዚሁ ፡ ለተዝከራቸው ፡ ያኖራሉ ። ምነው ፡ ዓይናቸው ፡ ሲያዩ ፡ ቢሰጡት ፡ ይከፋን ፡ ይሆን ።

እግዚአብሔር ፡ በጥበብ ፡ ሁሉን ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ አድርጎ ፡ ፈጠረ ፡ አስተውል ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ፀሐይንና ፡ ጨረቃን ፡ በጋንና ፡ ክረምትን ፡ ቀንንና ፡ ሌሊትን ፡ ሰውንና ፡ መላእክትን ፡ አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ ጻድቅንና ፡ ኃጥኣን ፡ ይህችን ፡ ዓለምና ፡ የወዲያኛይቱን ፡ ዓለም ።

ከስካር ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከመዋል ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ መጾም ፡ ይሻላል ። አሸን ፡ በክረምት ፡ ወራት ፡ በአንዲት ፡ ሰዓት ፡ ከጕድጓዱ ፡ ወጥቶ ፡ በክንፉ ፡ እንዲበር ፡ በ፪ተኛው ፡ ሰዓት ፡ ክንፉ ፡ ረግፎ ፡ በእግሩ ፡ እንዲሄድ ፡ ወፍም ፡ እንደሚበላው ፡ የዚህም ፡ ዓለም ፡ ተድላውና ፡ ደስታው ፡ ክብሩም ፡ እድሜውም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

የእሳት ፡ ራት ፡ ዙራ ፡ ፈልጋ ፡ ከእሳት ፡ እንደ ፡ ምትገባ ፡ ኃጥአንም ፡ ዲያብሎስን ፡ ዙረው ፡ ፈልገው ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ይገባሉ ። መልክምን ፡ መብል ፡ መልክምን ፡ መጠ



ጥ ፡ ዓሊምንም ፡ ሁሉ ፡ በወዴት ፡ ምን ፡ ይሆናል ። ሞት ፡ ድንገት ፡ መጥቶ ፡ አስጨንቆ ፡ በግድ ፡ ይወስዳልና ።

እሳት ፡ በእንጨት ፡ ነዶ ፡ እንዲገለጥ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በጻድቃን ፡ ላይ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። ጉሽ ፡ ጠላና ፡ ያልፈላ ፡ ወጥ ፡ ልብ ፡ እንዲያተኩስ ፡ ሳይሰፍሩ ፡ ሳይቆጥሩ ፡ ያኖሩትም ፡ ገንዘብ ፡ እንዲዚያ ፡ ነው ፡ ሰውንም ፡ ያሳማል ።

መሬት ፡ መሬትን ፡ ይበላዋል ። የሴት ፡ ልብ ፡ ቀላይ ፡ ባሕር ፡ ነው ፡ አቅፏት ፡ ከሚተኛ ፡ በቀር ፡ ማን ፡ ያውቀዋል ፡ ብልሐተኞች ፡ ሰዎች ፡ እሳትንና ፡ ነፋስን ፡ ወሀንም ፡ በመዘውር ፡ ይዘው ፡ ሲያሰሯቸው ፡ ይኖራሉ ፡ ደመወዛቸውን ፡ እንኳ ፡ አይሰጧቸውም ፡ አይከፋን ፡ ይሆንን ።

ከምጣጣ ፡ ጠላ ፡ መጠጣት ፡ ጅማት ፡ ያሰቅቃል ፡ የክፉ ፡ ሰውም ፡ ነገር ፡ አንጀት ፡ ይበጥሳል ። መርከብ ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ ሲሄድ ፡ ድንገት ፡ ድንጋይ ፡ እንዲያፈርሰው ፡ ንጉሥም ፡ በሠራዊቱ ፡ ላይ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ፡ መንግሥቱን ፡ በበደለ ፡ ጊዜ ።

እንጨትና ፡ ሣር ፡ ዝናም ፡ አብቅሏቸው ፡ አንዱ ፡ በጥ ፡ አንዱ ፡ ግድግዳ ፡ እየሆኑ ፡ እናስገባም ፡ ይሉታል ። መናፍቃንም ፡ የፈጠራቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ለፍጡር ፡ ይሰግዳሉ ።

ነገሥታትና ፡ መምህራን ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ መልክም ፡ ቢሆኑ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ወንጌል ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ በተሰበከ ፡ ነበር ። የውሀም ፡ መልክምነቱ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ በፈሰሰ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉን ፡ አብቅሎ ፡ ምግብና ፡ ልብስ ፡ ይሆናል ፡ ዱቄቱን ፡ አርሶ ፡ እንጀራ ፡ ያደርገዋል ፡ የደረቀውን ፡ እርሾ ፡ ለስላሳ ፡ ያደርገዋል ፡ ያደፈውን ፡ አጥቦ ፡ ንጹሕ ፡ ያደርገዋል ። ከጠጅና ፡ ከጠላ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጣማቸውንና ፡ ሽታቸውን ፡ ያሰምረዋል ፤ መምሕሩንም ፡ እ ንደዚህ ፡ ቢሆኑ ፡ ዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አክል ፡ አንድ ፡ አምሳል ፡ አንድ ፡ ነፍስ ፡ በሆነ ፡ ነበር ።

ዓሣ ፡ ከውሀ ፡ ውስጥ ፡ ከመኖር ፡ መሬትና ፡ ዴንጊያ ፡ ከመላስ ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ መጥቶ ፡ ጨውና ፡ ቅቤ ፡ አይበላ ምን ፤ ቆቅስ ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ መጥታ ፡ ብትመረቅ ፡ ሁብት ፡ አግኝታ ፡ እንጀራ ፡ በልበላችምን ፡ ጥሬ ፡ ሲፈልጉ ፡ ከመኖር ።

ዘንዶ ፡ ቢረዝም ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ይጠቀማል ፤ የሰይጣን ፡ ማደሪያ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ እግርና ፡ እጅ ፡ እንኳ ፡ የለውም ። መናፍቃንስ ፡ ቢበዙ ፡ ብልሀት ፡ ሳይኖራቸው ፡ ምን ፡ ይሆናሉ ። እናንት ፡ ሰነፎች ፡ ድንቁርናን ፡ ከማይመለስበት ፡ ሽጡት ፡ የሰነበተ ፡ እንደሆነ ፡ ይገድላችኋልና ።

ስብ ፡ ቢያጤሱት ፡ ይሸታል ፤ ብልሀትም ፡ ቢያበዙት ፡ ያከብራል ። ሰልፍን ፡ መነኩሴ ፡ ያውቃል ፤ ዝንብን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በጭራ ፡ ዓይን ፡ ዓይኗን ፡ ይላታልና ። ዕውር ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ መልከም ፡ ወጥ ፡ የቀመሰ ፡ እንደሆነ ፤ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያው ፡ ይመስለዋል ።

አንበሳ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረውን ፡ ምን ፡ ቸገረኝ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ ነፍስ ፡ ካልገደለ ፡ የማይበላ ።

ላምና ፡ በግ ፡ ጠጉርና ፡ ቁርበት ፡ ለብሶ ፡ ከመኖሩ ፤ ሸማና ፡ ግምጃ ፡ ከለበሰው ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ በቅቤና ፡ በጨው ፡ ታፍኖ ፡ መኖር ፡ አይሻላቸውምን ። ዶሮስ ፡ ይህ ፡ ከስኳሳ ፡ ሸቀናም ፡ ጠጉር ፡ ምን ፡ ይሆናታል ፤ ድልህና ፡ ቅቤ ፡ አጥግቤ ፤ በሞቀ ፡ ወሀ ፡ አጥቤ ፡ ከሚሞቅ ፡ ቤታ ፡ ብከታት ፡ አይሻላትምን ።

ዓሣስ ፡ ከውሀ ፡ ውስጥ ፡ መኖሩ ፡ ምን ፡ እጠቀም ፡ ብሎ ፡ ነው ፤ እንደኔስ ፡ ቢሆን ፡ ከብርድ ፡ ስፍራ ፡ መኖር ፡ እጅግ ፡ ያሳ ዝነኛልና ፡ አጥቤ ፡ እንዲሞቀው ፡ ከእሳት ፡ ዳር ፡ ባደረኩት ፡ ነበ ር ። በወደደው ፡ ልክ ፡ ጨውና ፡ ቅባኑግም ፡ አጠግበው ፡ ነበር ።



ሎሚ ፡ ሲያብብ ፡ ይኖራል ፤ መልካም ፡ ይሸታል ፤ መ ከምጠጡን ፡ ከልተወ ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ ፊት ፡ ያጠቁ ራልና ። ጆብ ፡ ያህያ ፡ ሥጋ ፡ በጠገበ ፡ ጊዜ ፤ ጨኸቱ ፡ ከነገር ፡ አያስቀምጥም ።

የነብር ፡ ቁርበት ፡ ከበረት ፡ ቢሰቀል ፡ ፍየሎች ፡ ይ ደነግጋሉ ። ብርቱም ፡ ንጉሥ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ መናፍቃን ፡ ይታወከሉ ። የንጉሠን ፡ ዘር ፡ ቢዘሩት ፡ ሰናፍጭ ፡ አይሆንም ፤ ሰውንም ፡ አንተ ፡ በሬ ፡ አንተ ፡ ጋላ ፡ ብለ ፡ ቢሰድቡት ፡ የአዳም ፡ ልጅ ፤ መሆኑን ፡ አይተውም ።

ፋቅር ፡ ቢያረጅ ፡ ቀርፍት ፡ ይሆናል ፡ ( ይይዛል) ምነው ፡ ቢሉ ፡ ተቀርፎ ፡ ሊወድቅ ፡ ከመልካም ፡ ከታላቅ ፡ ወንዝ ፡ ከለመለመ ፡ ብትደርስ ፡ ተጠንቀቅ ፤ ከዚያ ፡ የሚመጣው ፡ ብዙ ፡ ነውና ።

መልከም ፡ ቆንጆ ፡ አመንዝራ ፡ ሴት ፡ ካለችበት ፡ ቤት ፡ አትግባ ፤ በከንቱ ፡ እንዳትሞት ። ሴት ፡ ከመሆን ፡ ወንድ ፡ መሆን ፡ ይሻላል ። እንስሳ ፡ ከመሆን ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ ይሻ ላል ። ደንቆሮ ፡ ከመሆን ፡ ብልህ ፡ መሆን ፡ ይሻላል ።

መላጣ ፡ ሰው ፡ የፀሐይ ፡ ወዳጅ ፡ ነው ፤ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ያሳያታልና ። ጠጉራም ፡ ሰው ፡ ያስቀይማታል ፤ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ጠጉሩን ፡ ያንጨፈርርባታልና ። ነጭ ፡ ሽንኩርት ፡ ምነው ፡ ይሸታል ፡ ይተኩሳል ፡ ቢሉ ፡ እርሱማ ፡ የጠባዩን ፡ ክፋት ፡ አውቆ ፡ እራሱን ፡ ወደምድር ፡ ቀብሮ ፡ እኖራለሁ ፡ ቢል ፡ ና ፡ ውጣ ፡ እያላችሁ ፡ እናንተ ፡ ብታሳድዱት ፡ ምን ፡ ትጠቀሙላችሁ ።

ማሽላን ፡ ወፎች ፡ እራስ ፡ እራሱን ፡ ሲሉት ፡ አይቶ ፤ ባቄላ ፡ ፍሬውን ፡ በገንኑ ፡ አዝሎ ፡ ክንፉን ፡ አልብሶ ፡ ይኖ ራል ። ወሀ ፡ ወርዶ ፡ ወርዶ ፡ ባይመቸው ፡ ኩሬ ፡ ይሆናል ። ብልህ ፡ ሰው ፡ በጨነቀው ፡ ጊዜ ፡ ሞኝ ፡ ይሆናል ።

www.ethiopianorthodox.org

ገዶ ፡ አሞሬ ፡ እርሷ ፡ ያልገደለችውን ፡ ሥጋ ፡ አትበላም ፤ መልክም ፡ ሰው ፡ ያለገንዘቡ ፡ አይነካም ። ረሀብ ፡ ውሎውና ፡ አዳሩ ፡ ከማነው ፤ ሥራ ፡ ከማይወድ ፡ ከኩሩ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ ጥጋብ ፡ ውሎውና ፡ አዳሩ ፡ ከማነው ፤ ከሠራተኛና ፡ ከቸር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ነው ። ሰይጣንስ ፡ አዳሩና ፡ ውሎው ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ከልበ ፡ ጠማማና ፡ ከዕቡይ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ነው ። ከለውና ፡ ከሞተው ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ይበልጣል ፤ የሚያምለውንና ፡ የሚገዘተውን ፡ ሰው ፡ ጨዋምር ፡ የሞተው ፡ ይበልጣል ፤ ስግብግብ ፡ ሰው ፡ ለመብል ፡ የሚጣደፍ ፡ ሆዱ ፡ አምላኩ ፡ ነውና ፤ ቃላቅ ፡ ጉርሻ ፡ ጕርሶ ፡ አንቆት ፡ ወይም ፡ ሆዱን ፡ ነፍቶት ፡ ቁንጣን ፡ ይገድለዋል ።

ጨለማ ፡ እጅግ ፡ ጠላቶችን ፡ ሆኖ ፡ ገና ፡ ሳንተያይ ፡ ፊቱን ፡ ያጠቁሬልና ፤ ሥራችሁንም ፡ አትሥሩ ፡ ይላል ፤ እርሱ ፡ የሰንበት ፡ ሹም ፡ መሆኑ ፡ ነውን ፡ እርስ ፡ በርሳችሁም ፡ አትተያዩ ፡ ይላል ፤ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፤ ዘመድ ፡ አላጣንም ፡ የብርሃን ፡ ልጆች ፡ ነን ። ሁሉንም ፡ እናሳድምና ፡ ፀሐይና ፡ ጨረቃን ፤ ከዋክብትንም ፡ በሬት ፡ ማጠሙት ፡ ብለን ፡ በኋላው ፡ እሳትን ፡ እንልቀቅበት ። ዓይናችንም ፡ ዘወትር ፡ ጠላቱን ፡ ከማየት ፡ ይረፍ ።

ሱፍ ፡ አበባውን ፡ አሳምሮ ፡ አሾሁን ፡ አጥሮ ፡ ይኖራል ። ምነው ፡ ቢሉ ፤ የአዳም ፡ ልጆች ፡ ጉምጁዎች ፡ ናቸውና ፡ ዘለው ፡ እንዳይዙት ፡ ነው ። አሁን ፡ ቢጮሁ ፡ አጣጥና ፡ ግራር ፡ ባልረዱዋቸውምን ፤ እረ ፡ ገና ፤ እነዚህ ፡ ፍሬ ፡ ቢሶች ፤ ተገትረው ፡ የቀሩትን ፡ ምን ፡ ጣም ፡ አላቸው ፡ ብለህ ፡ ነው ። ከሞር ፡ ገንዘብ ፡ ሲወድ ፡ ነፍስም ፡ የለው ፤ ዘወትር ፡ የሚገኘው ፡ ከወርቅ ፡ ቤት ፡ ነውና ፤ ያጠመደ ፡ አያጣውም ። ሥጋም ፡ ፍራቱን ፡ እጅግ ፡ አበዛው ፤ ከቃረደ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ያንቀጠቅጠዋል ፤ ምንስ ፡ ያንበደበደዋል ።



## መጽሐፈ ፡ ጨዋታ ፡ መንፈሳዊ ።
## ክፍል ፡ ፩ ።

ቅቤ ፡ ለመጽሐፍ ፡ ዘመዱ ፡ አይደለም ፤ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ቅቤ ፡ ነው ፤ አታክልት ፡ ሆኖ ፡ ከላፈረ ፤ ሰው ፡ ሆኖ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከልፈራ ፡ መቆረጥ ፡ አይቀርለትም ። ክትኳችና ፡ አረሚ ፡ የሌለው ፡ አትክልት ፡ አይረባም ። ንጉሥና ፡ መምሕር ፡ የሌላትም ፡ አገር ፡ እንደዚህ ፡ ናት ፤ ኃጢአት ፡ ስትሠራ ፡ ያስ ፡ ይላታል ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ፍሬ ፡ ስታፈራ ፡ ፍሬዋ ፡ እሬት ፡ ይሆናል ።

ከረጢት ፡ መሰፋቱ ፡ የወርቅ ፡ መያዣ ፡ ነው ፤ የሰው ፡ ልብም ፡ መፈጠሩ ፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ ለማወቅ ፡ ነው ። የጃርት ፡ ልብሷ ፡ እሾህ ፡ ነው ፤ የዲያብሎስም ፡ ልብሱ ፡ ክፋት ፡ ነው ።

ሽንኩርትና ፡ ድንች ፡ ፍሬያቸው ፡ በሥራቸው ፡ እንደ ሆነ ፤ ጻድቃንም ፡ በሥራቸው ፡ ለማፍራት ፡ የአምላካቸውን ፡ ነገር ፡ በልባቸው ፡ ይተክላሉ ።

በገና ፡ ሆዱ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ለወፍራሙም ፡ ለቀጭኑም ፡ እንደ ፡ ጠባያቸው ፡ እንደሚጮህ ፤ እግዚአብሔርም ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ ለፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደጠባዩ ፡ እንደ ፡ ጠባዩ ፡ ይሰጠዋል ።

የተምር ፡ ፍሬ ፡ እንዲጣፍጥ ፤ የጻድቃንም ፡ ሥራ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ፡ ቅል ፡ በዝናም ፡ ይበቅላል ፤ ሾከላም ፡ በውሃ ፡ ይሠራል ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ ለወሀ ፡ ማደሪያ ፡ ይሆናሉ ።

ሰውንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፈጠረው ፡ በኋላ ፤ መልክም ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ማደሪያው ፡ ያደርገዋል ። መሳል ፡ መልክም ፡ ነው ፤ ብረትን ፡ ይስለዋልና ፤ መጽሐፍም ፡ መልክም ፡ ነው ፤ ልብን ፡ ያበራዋልና ።

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር፡ እድሜ፡ አረጀ፤ ዘመኑንም፡ የሚያውቀው፡ ታጣ። መጽሐፍ፡ መንጽር፡ ነው፤ ለሚመለከተው፡ ሰው፡ ከኍቅ፡ ያሳያልና። ሰነፍ፡ ሰው፡ በሰው፡ ይታመናል፤ ኋላም፡ ተመልሶ፡ ጠላት፡ ይሆንዋልና፡ ምንም፡ አያገኝ፤ እግዚአብሔርን፡ ግን፡ ተስፋ፡ የሚያደርግ፡ ሁሉን፡ ያገኛል።

በጥቂት፡ ደመና፡ የደጋ፡ መሬት፡ በረዶ፡ እንደሚያፈላ፤ እግዚአብሔርንም፡ በማይፈራ፡ ሰው፡ መከራ፡ ድንገት፡ ይደርስበታል።

ነብር፡ ፍየልን፡ ተኵላ፡ በግን፡ ድብ፡ አህያን፡ ሞጭሞጭላ፡ (ምጥማጥ፡) ዶሮን፡ እንደሚፈልጉ፡ ዲያብሎስም፡ የአዳምን፡ ልጆች፡ እንደዚያ፡ ይፈልጋቸዋል።

የወጥ፡ ማጣፈጫው፡ ምንድር፡ ነው፡ ጨውና፡ ቅቤ፤ የሰውም፡ ማጣፈጫ፡ ሃይማኖትና፡ ምግባር፡ ነው፤ የእግዚአብሔርን፡ ትእዛዝ፡ ከማፍረስ፡ አሬት፡ መብላት፡ ይሻላል። ምነው፡ ቢሉ፤ በውሀና፡ በማር፡ ይሟሻልና። የእግዚአብሔርን፡ ትእዛዝ፡ ግን፡ ያፈረሰ፡ ዘለዓለም፡ እንደ፡ መረረው፡ ይኖራል።

እግዚአብሔር፡ አብ፡ ማት፡ ነው፡ እግዚአብሔር፡ ወልድ፡ ብዕር፡ ነው፤ እግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ቀለም፡ ነው፤ ሰማይና፡ ምድር፡ ወረቀት፡ ናቸው፤ ፊደሉም፡ ፍጥረት፡ ነው፤ እግዚአብሔር፡ አብም፡ በቃሉ፡ ሰማይንና፡ ምድርን፡ ፈጠረ፤ ያለበቸውንም፡ ፍጥረት፡ ሁሉ፡ ፈጠረ፤ በመንፈሱም፡ አጸናቸው።

የወጥ፡ ማጣፈጫው፡ ምንድር፡ ነው፡ ጨውና፡ ቅመም፡ ቅቤም፡ ነው፤ የሰውም፡ ማጣፈጫው፡ ሃይማኖትና፡ ፍቅር፡ ነው፤ ሃይማኖት፡ ያለው፡ ሰው፡ ሁሉን፡ ያገዝዛል፤ ኤልያስ፡ ሰማይን፡ ሶስት፡ ዓመት፡ ከ፮ወር፡ ዘጋ፡ ዝናብም፡ አልዘነበም። ቀለም፡ በቀንድ፡ (በብልቃጥ፡)



ሳለ፡ ጨለማ፡ ነው፤ በተጻፈ፡ ጊዜ፡ ግን፡ ብርሃን፡ ነው።

ቀለም፡ በቀንድ፡ ሳለ፡ ድዳ፡ ነው፤ በተጻፈ፡ ጊዜ፡ ግን፡ መላሰኛ፡ ነው። ቀለም፡ በቀንድ፡ ሳለ፡ ጭምት፡ ነው፡ በተጻፈ፡ ጊዜ፡ ግን፡ እንደሰከረ፡ ነው። ሁሉንም፡ ያለፈልፋል።

የንጉሥም፡ ልጅ፡ እደዚህ፡ ነው።

የዚህን፡ ዓለም፡ ሥራን፡ አገኘለሁ፡ ብዬ፡ ቆፈርሁት፡ ጾጉም፡ ድንጋይ፡ ሆነብኝ፤ ድጅና፡ አሳቤም፡ ሁሉ፡ አለቀ፤ እንዲያውም፡ በየው፡ በስተውለው፡ ሥራ፡ እግዚአብሔር፡ ነው።

ጨረቃ፡ አንድ፡ ጊዜ፡ እንድትጎድል፡ አንድ፡ ጊዜ፡ እንድትሞላ፤ የዚህም፡ ዓለም፡ ንብረት፡ እንደዚህ፡ ነው፤ ፀሐይ፡ ሙሉ፡ እንደሆነች፡ ብርሃኗም፡ ሙቀቷም፤ የወዲያውም፡ ዓለም፡ እንደዚህ፡ ነው። የሰው፡ ልቡ፡ ፊደል፡ ነው፤ ያሰበውንና፡ የተናገረውን፡ የሰማውንም፡ ለቅሞ፡ ያኖራልና።

እሳት፡ ንጉሥ፡ ነው፤ ጢስ፡ ጭፍራ፡ ነው፤ እሳት፡ ንጉሥ፡ ቢያቃጥል፤ ጢስ፡ ጭፍራ፡ ያፍናል።

ከበላይና፡ ከዶኝ፡ ከእንጨቱም፡ እሳት፡ ወጥቶ፡ እንዲቃጠል፤ ጻድቃንም፡ ቢቆጡ፡ እሳት፡ ይዘንማል። ሙሽራ፡ በጫጉላዋ፡ ውስጥ፡ እንደምታምርና፡ ደስ፡ እንደምታሰኝ፡ ጻድቃንም፡ በመንግሥተ፡ ሰማያት፡ እንደዚያ፡ ናቸው።

ጻሐፊ፡ ሰው፡ የማትረባውንና፡ የማትጠቅመውን፡ ደብዳቤ፡ ጠቅልሎ፡ ከእሳት፡ እንደሚጥል፤ እግዚአብሔርም፡ ይህን፡ ዓለም፡ ሲያሳልፍ፡ እንደዚያ፡ ነው።

በኖኅ፡ ጊዜ፡ የነበሩ፡ ሰዎች፡ ስለ፡ ዝሙት፡ አልተወደዱም፡ ወሀ፡ ሆነው፡ ቀሩ፡ እንጂ፤ በሰዶም፡ ዝሙት፡ ግን፡ የሎጥ፡ ሚስት፡ ጨው፡ ሆና፡ ቀረች።

ፀሐይ፡ ለኢየሱ፡ ስለምን፡ ቆመችለት፡ መድኃኒቱን፡ ኢየሱስን፡ መስሏት፡ ይሆን፤ ኢየሱስ፡ መድኃኒቱ፡ ሰውም፡ አይገድል፡ ያድናል፡ እንጂ።

www.ethiopianorthodox.org

መድፍ፡ሸክሙ፡የከበደ፡ነው። ነገር፡ግን፡በመንኰራኵር፡ይሄዳል። ሰልፍም፡ለጊዜው፡የሚያስፈራ፡ግሩም፡ግሙንቅ፡ነው። ማሸነፍ፡ግን፡በሀብት፡ነው፡እንጂ፡በጉልበት፡አይደለም።

በለዓም፡እስራኤልን፡ለመርገም፡ለምን፡ይሄዳል፡ምርቃትን፡ያዕቆብ፡ሠርቶ፡እንዳመጣት፡አያውቅምን፡አህያይቱ፡እንኳ፡ከለከለችው፡ለካ፡በጊዜው፡መሥረቅ፡መልክም፡ነው። ኮከብ፡ከያዕቆብ፡ሲወጣ፡አየሁ፡ይላል፡ያዕቆብን፡ሰማይ፡ማድረጉ፡ነውን።

ባላቅስ፡በጉን፡ለምን፡በየተራራው፡ይፈጃል፡ያዕቆብ፡እንደሆነ፡የበግ፡ለምድ፡ለበሰ። ቀስ፡ብሎ፡ገብቶ፡ከኤሳው፡የነጠቃት፡ምርቃት፡ናት።

እንዲያውስ፡ፈጣሪውን፡ሌሊት፡ሁለት፡ጊዜ፡ቃጣሎ፡የማለ፡አይደለምን፡ፈጣሪውን፡ያሸነፈውን፡እኔ፡እችላለሁ፡ብሎ፡ነውን፡ደግሞስ፡ያማቱን፡በንች፡እንጨት፡አዝንርጉሮ፡እያሳየ፡ገና፡በማሕፀን፡ሳሉ፡ዝግርጉር፡እያደረገ፡ለቅም፡የወሰደበት፡እርሱ፡አይደለምን፡ወንድሙንስ፡ገና፡በማሕፀን፡ሳለ፡ያሰነከለ፡እርሱ፡አይደለምን፡ባላቅ፡ሆይ፡ተው፡ይህ፡ሰው፡ረቂቅ፡ደጅን፡ይኖረዋል፤ልያስ፡ከራሔል፡ጋራ፡ሃምን፡ያማላታል፤ወይስ፡እንደ፡ሎጥ፡ሚስት፡ጨው፡መሆን፡ይፈልጋታልን፤ስለ፡ዝሙት፡ይልቅ፡በልጁዋ፡እንከይ፡መማዘት፡ይሻላታል፤ሎጥ፡ልጆቹን፡የደገማቸው፡እንደ፡እናታቸው፡ጨው፡ይሁኑ፡ብሎ፡ነውን።

---

## መጽሐፈ፡ጨዋታ፡ወንጌላዊ።
### ክፍል፡፩።

እግዚአብሔር፡በደብረ፡ሲና፡በጄ፡አሥር፡ነገር፡ዘራ፤የሚያጭደውም፡በቃጣ፡ጊዜ፡አንድ፡ልጁን፡ቢልክው፡እንግዳ፡ነውና፡በዳዊት፡ቤት፡አደረ፤ይህንም፡አዝመራ፡፴፫፡ዓመት፡ሙሉ፡ብቻውን፡አጭዶ፡በጨረሰ፡ጊዜ፤አባቱ፡አበቱ፡አመስግኑኝ፡አለ፤ምነው፡ከረኛ፡ቤት፡ተወለደ፡ብለን፡አምተነው፡ነበር፤አሁንስ፡እርሱ፡ራሱ፡እረኝነቱን፡ገለጠው፤ለካ፡የበጎች፡እረኛ፡እኔ፡ነኝ፡እያለ፡ከሰማይ፡ተሰዶ፡የመጣ፡በጎችን፡ሊጠብቅ፡ነውን።



ከሰማይ፡ድረስ፡መጥቶ፡በግ፡መጠበቅ፡ከልቀረለት፡ይህችን፡ቃናስ፡መንጋ፡መጠበቁ፡ለምንድር፡ነው፡ከምድር፡ዳር፡እስከ፡ምድር፡ዳር፡ድረስ፡ያለውን፡መንጋ፡አንድ፡አድርጎ፡ጠብቆ፡ደመወዙን፡በምስጋና፡አውጥተን፡እንሰጠውምን።

የተሰበረውን፡ጠግኖ፤የደከመውን፡አሳርፎ፤ተኩላ፡እንዳይነጥቃቸው፡ጠብቆ፤ከበጎቹስ፡መልካካሙን፡እየመረጠ፡አይወስድምን። ቀበሮውንስ፡ያውቀው፡የለምን፤አንድ፡በግ፡ባገኘ፡ጊዜ፡ይዞ፡ወደ፡ጉድጓድ፡እንደሚገባ።

ያችም፡በግ፡ከረኛዋ፡ፈቃድ፡ወጥታ፡ከተገኘች፡መዳን፡የላትም። ምነው፡እርሱ፡ባዘዘት፡ብትገባ፡ደጁ፡እርሱ፡አይደለምን። አዳምንና፡ሔዋንን፡የኃጢአት፡ብርድ፡ቢያንቀጠቅጣቸው፡ክርስቶስ፡ሥጋን፡ለበሰ።

በበረትም፡ወድቆ፡ወገኖቹ፡የላም፡እረኞች፡አዩት፤ለላም፡እረኞችም፡የምስራች፡ነገራቸው፤ለካ፡እረኛ፡እረኛ፡ነው።

---

### ክፍል፡፪።

በ፭ሺ፡አምስት፡መቶ፡ዘመን፡እግዚአብሔር፡እጅግ፡ተዋረደ፤አንድ፡ልጁን፡ለሰው፡ባሪያ፡ሆነህ፡ሥጋ፡

www.ethiopianorthodox.org

ተሸክም ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ። ወዮ ፤ ወዮ ፤ ወዮ ፡ ዋ ፡ ዋ ፡ ዋ ፡ መላእክትስ ፡ ጌታ ፡ የሰው ፡ ሥጋ ፡ ሲሸከም ፡ እያዩ ፡ ቆመው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ማየታቸው ፡ ለምንድር ፡ ነው ። የሥጋ ፡ መብል ፡ ስለአለበት ፡ ሁሉም ፡ የምድሬቱን ፡ ኑሮ ፡ ወደዱ ። በሰማይስ ፡ ሥጋም ፡ ጠጅም ፡ የለም ፡ አሉ ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ባዶ ፡ አገር ፡ መላእክትን ፡ እከክ ፡ አይቆረርጣቸውምን ።

የእግዚአብሔርስ ፡ ልጅ ፡ ከእብቱ ፡ ጉያ ፡ ተለይቶ ፡ የመጣ ፡ ለሥጋ ፡ ንጉቶ ፡ አይደለምን ። ከሰማይ ፡ ድረስ ፡ ተሰዶ ፡ መምጣቱ ፡ ሁብት ፡ ሆኖት ፡ መቸም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብላ ፡ ብሎ ፡ ታል ። ዕለቱን ፡ እንደመጣ ፡ ከዳዊት ፡ ቤት ፡ በሥጋ ፡ አደረ ።

ምነው ፡ አብና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቀሩ ። ሥጋ ፡ አይደም ራቸውምን ፤ እንኳን ፤ ልጅ ፡ ለሥጋ ፡ ስሱ ፡ ስለሆነ ፡ ተቀለ ብልቦ ፡ መጣ ፡ እንጂ ፤ ሁለቱስ ፡ እሳት ፡ ናቸው ። ጥበባቸ ውም ፡ አይታወቅ ። ይልቁንስ ፡ ልጅየው ፡ ዘመዶችን ፡ ነው ። ሁሉንም ፡ አጫውቶናል ። የርሱስ ፡ ዝምድና ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ የዚያው ፡ ልጅ ፡ ከዚያው ፡ ነው ፡ ዘረው ፡ ዘረ ው ፡ አንድ ፡ ናቸው ። ብሎም ፡ የዘመድ ፡ ዘመድ ፡ ወንዝ ፡ ያሻግራል ፡ እንዲሉ ፡ ሁሉንም ፡ እናምናቸዋለንና ፡ አይቶ ውንም ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

ማርያም ፡ ሰማይን ፡ መሰለች ፡ ከቶ ፡ እሳቱ ፡ እጥቁ ሯት ፡ ይሆን ። አይሁድ ፡ ቀን ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፤ በምድር ፡ ሲ ሄዱ ፡ የተናቀው ፡ ደንጊያ ፡ እንቅፋት ፡ ሆነባቸው ፤ ምነው ፡ አስተውለው ፡ ቢሄዱ ። ኒቆዲሞስ ፡ ግን ፡ በሌሊት ፡ ሲሄድ ፤ በውሀ ፡ ውስጥ ፡ መንገድ ፡ አገኘ ። ወህም ፡ ከ፰ሺ ፡ ከ፷፻ ፡ ዘመን ፡ መክና ፡ የነበረች ፡ አሁን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ወለደች ።



ከቶ ፡ ልጅነት ፡ አይቀርም ፡ ኢየሱስ ፡ ከዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ እጫወት ፡ ብሎ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፤ በር ሱም ፡ ድንጋጤ ፡ ሰማይ ፡ ተከፈተ ። አባቱም ፡ ከላይ ፡ ሆኖ ፡ ልጄ ፡ ወዳጄ ፡ ሲል ፡ ዋለ ። መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ርግብ ፡ ሆኖ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ዋለ ። ዮሐንስ ፡ እነሆ ፡ የእግዚ አብሔር ፡ በግ ፡ እያለ ፡ ለምን ፡ ያሳየዋል ፤ ያለጊዜው ፡ ይ ታረድ ፡ ብሎ ፡ ነውን ። ቢታረድስ ፡ የታደሉና ፡ የተመረጡ ፡ ጆሮች ፡ ይበሉታል ፡ እንጂ ፡ ፈሪ ፡ አይበላውም ። እር ሱም ፡ ምሥጢር ፡ አይችልም ፤ ብናበላው ፡ ብናጠጣው ፡ ከብቱ ፡ ዘንድ ፡ የየውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረን ።

ለቀበሮች ፡ ጉድጓድ ፡ አላቸው ፤ ለሰማይ ፡ ወፎችም ፡ ማ ረፊያ ፡ ዛፍ ፡ አላቸው ፤ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ እራሱን ፡ የ ሚያስጠጋበት ፡ የለውም ፡ ይላል ። ለካ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ቢጠበው ፡ ነው ፡ ከሰው ፡ ውስጥ ፡ መጥቶ ፡ ያደረ ፤ እንደ ባሪያም ፡ ደምሰለ ።

ኢየሱስ ፡ ሥርግ ፡ ቢጠሩት ፡ በቃና ፡ ዘገሊላ ፡ ወሀው ን ፡ ጠጅ ፡ አድርጐ ፡ አጠጣ ፤ በሰው ፡ ሥርግ ፡ እንደዚህ ፡ የ ሆነ ፡ በራሱ ፡ ሥርግ ፡ እንዴት ፡ ይሆን ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ ሥርግ ፡ አይቼ ፡ ከድግሱም ፡ በልቼ ፡ ጠጥቼ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ምነው ፡ በሞትሁ ።

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኑ ፡ ያባቴ ፡ ቡሩካን ፤ ዓለም ፡ ሳይ ፈጠር ፡ የተዘጋጀላችሁን ፡ ውረሱ ፡ ይላል ፤ ዓለም ፡ ሳይፈ ጠር ፡ ምን ፡ ኖሮታል ፡ ጥበቡ ፡ አይታወቅ ።

## ክፍል ፡ ፭ ።

እናንት ፡ የዓለም ፡ ብርሃን ፡ ናችሁ ፡ አለ ፡ መብራት ኢብርቶ ፡ በእንቅብ ፡ ውስጥ ፡ የሚያኖር ፡ የለም ፡ ይላል ። ዓለምን ፡ ያህል ፡ እንቅብ ፡ ደፍቶብን ፡ የለምን ፤ እኛ ፡ በወ

www.ethiopianorthodox.org

ዴት ፡ እናብራ ። ጳውሎስስ ፡ እንኳ ፡ እስከ ፡ እድሜው ፡ ልክ ፡ አበራ ።

አንተ ፡ ነጋዴ ፡ እያላችሁ ፡ ለምን ፡ ትሳደባላችሁ ፡ ገበያ ፡ ተደመቀ ፡ ምን ፡ ደኅና ፡ አለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የበለጠስ ፡ ምን ፡ ንጉሥ ፡ አለ ፡ ገበያ ፡ ቢያመጣቸው ፡ ፩ ፡ ልጁን ፡ ለዓለም ፡ አለወጠጠውምን ፡ ዮሴፍንስ ፡ ወንድሞቹ ፡ ለ፴ ፡ ብር ፡ አልሸጡትምን ፡ ከተሸጠ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለምድረ ፡ ግብጽና ፡ ለከነአን ፡ አገር ፡ የራብ ፡ መድኀኒት ፡ ሆነ ።

እንጸሳ ፡ ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ዱር ፡ ገበ ፡ ምን ፡ እንስሳ ፡ ይሰብር ፡ ይሆን ፡ ከዲያብሎስ ፡ በቀር ። እንዚያ ፡ አራቱ ፡ መላእክት ፡ እንስሶች ፡ ናቸው ፡ ከጀርባቸው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ፍም ፡ መጥቶ ፡ ተሰው ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ አለመናገራቸው ፡ ከነዚህስ ፡ ገብርኤል ፡ ይሻላል ፡ ተሸቀዳድሞ ፡ መጥቶ ፡ ለቆንጆዩቱ ፡ የነገረልን ።

የሰማይ ፡ እሳት ፡ ከሰው ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ አለማቃጠሉ ፡ ምንድር ፡ ነው ። ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅስ ፡ ገንዘባችሁን ፡ እየሰበሰባችሁ ፡ ወደሰማይ ፡ ላኩ ፤ ከዚያ ፡ ይቆያችኋልና ፡ ይለናል ። ለካ ፡ የርሱ ፡ ገንዘብ ፡ አልበቃው ፡ ቢል ፡ ወደኛ ፡ ልጁን ፡ የላከ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ገንዘባችንን ፡ በብልሀት ፡ እንዲያከማች ፡ ኖሯል ። እንግዴህ ፡ አውቀንበት ፤ ገንዘባችንንም ፡ አናባክን ፤ ከሰማይስ ፡ እኛ ፡ ምን ፡ አለን ፤ ገንዘባችንን ፡ ወደዚያ ፡ አሸክመን ፡ ከምንልክ ፡ እንከሶችን ፤ እውሮችን ፤ ችጋረኞችን ፡ ወንድሞቻችንን ፡ ይዘን ፡ እንክት ፡ እያደረግን ፡ እንበላዋለን ፤ እንጠጣዋለን ፤ እንለብሰዋለን ፤ በገዛ ፡ ገንዘባችን ፡ ምን ፡ ይመጣብናል ። አላመጣችሁም ፡ ብሎ ፡ የሚያደርገውን ፡ እስቲ ፡ እናያለን ።



አብዮታችንን ፡ ከዚህ ፡ ቀድም ፡ አታሉ ፡ ያወጣው ፡ ገንዘብ ፡ ይበቃዋል ፡ ባለጠጋ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከሚገባ ፡ ግመል ፡ በመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ መሔድ ፡ ይሻላል ፡ ይላል ። ከርሱ ፡ የበለጠ ፡ ባለጠጋ ፡ አለን ፤ እርሱ ፡ በመንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ይኖር ፡ የለምን ፤ ይህንን ፡ እያመከኘ ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ አሸግሮ ፡ ማየቱ ፡ ምንድነው ፡ ከዚህ ፡ ቀድም ፡ አሥራትን ፡ ተናግሮ ፡ ተናግሮ ፡ ከወንጌል ፡ አደረሰን ፤ አታስቡ ፡ እያለ ፡ ገንዘባችንን ፡ ሊያስበላብን ፡ ወዲያው ፡ ተርቤ ፡ አላበላችሁኝም ። ተጠምቼ ፤ አላጠጣችሁኝም ። ታርዤ ፤ አላለበሳችሁኝም ። ታምሜ ፤ አላያችሁኝም ። እንግዳ ፡ ሆኜ ፤ አልተቀበላችሁኝም ። ታሥሬ ፤ አልጠየቃችሁኝም ፡ ይላል ። ይህን ፡ ያህል ፡ ስድስት ፡ ቃል ፡ ምን ፡ ያናግረዋል ። ወዲህ ፡ ለነገ ፡ አታስቡ ፡ ይላል ፤ ወዲህ ፡ አላበላችሁኝም ፡ ይላል ። ከኛ ፡ ወገን ፡ የተራበ ፤ የተጠማ ፤ የታረዘ ፡ የለም ፡ መስሎት ፡ ይሆን ፤ ተሰማይ ፡ ተሰዶ ፡ መጥቶ ፤ ተርቤአለሁ ፤ ተጠምቻለሁ ፤ ታርዣለሁ ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ ሰማይን ፡ ያህል ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ ይዞ ፡ አባቱ ፡ ከዚያው ፡ አያበላውም ፤ አያጠጣውም ፤ አያለብሰውም ፤ ልጁስ ፡ ሲቀላውጥ ፡ ነውር ፡ አይፈራምን ። እኛስ ፡ ለሰማይ ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ አናበላም ፤ አናጠጣም ፤ አናለብስም ፡ ከዚሁ ፡ ካሉት ፡ ከድሆች ፡ ወንድሞቻችን ፡ ጋራ ፡ ገንዘባችንን ፡ ተካፍለን ፡ እንበላለን ፤ እንጠጣለን ፤ እንለብሳለን ።

እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዘወትር ፡ ንዝንዝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ በወንጌል ፡ ገንዘባችንን ፡ ሊወርስ ፤ የጦም ፡ አዳር ፡ እያለ ፡ ሊከራለን ፡ አስቧል ፡ መሰል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፡ ፮ ።

እግዚአብሔር ፡ ፊሪ ፡ ነው ፡ እኛ ፡ ብንበድለው ፡ ልጁን ፡ ልክ ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ተዘምደህ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ በልጁ ታረቀን ፤ አሁን ፡ ምን ፡ ያደርገኝ ፡ መስሎት ፡ ነው ፡ ለክ ፡ በየቤቱ ፡ ፍራት ፡ አይታጣም ፡ እኛ ፡ ስለበደልነው ፡ የምንከሰውን ፡ እርሱ ፡ ከሰን ።

እንግዴህ ፡ ወዲህ ፡ ሥጋችን ፡ ከሆነ ፡ በሰበብ ፡ ባስባብ ፡ ብለን ፡ እርስቱን ፡ እንከፈለዋለን ፤ ጥቂት ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ መርፌ ፡ ትወጋ ፡ እንደሚሉት ፤ እንኳን ፡ ልጁን ፡ ልክ ፡ ተዛመደን ።

የክርስቶስ ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ አስቸገረ ፤ ልጅ ፡ ስለሆነ ፡ ይሆን ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተርቤ ፡ አላበላችሁኝም ፡ ይላል ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አምስት ፡ እንጀራ ፡ ለአምስት ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ አብልቶ ፡ አትርፎ ፡ ያስነሣል ።

ለበሬ ፡ ቀንድ ፡ አለው ፤ ለንጉሥም ፡ ዘውድ ፡ አለው ፡ ኧረ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምንሰጠው ፡ ክብር ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ አንለይለትምን ፤ አምልኮ ፤ ስግደት ፤ ምስጋና ፤ ለርሱ ፡ ነው ፤ በጣም ፡ እንገዛው ፤ እንለማመጠውም ። እንታጠቅለትም ። ታላቅ ፡ ጌታ ፤ ሰጪ ፡ ነሺ ፡ ነውና ።

አዳኝም ፡ ገዳይም ፡ እርሱ ፡ ነውና ። በሰማይና ፡ በምድርም ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ። ሁሉም ፡ ከርሱ ነው ፡ የተገኘው ፡ ሁሉም ፡ የሆነው ፡ በርሱ ፡ ነው ። አለርሱ ፡ ምንም ፡ የሆነ ፡ የለም ፡ ምስጋና ፡ ይገባዋል ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን ።

እግዚአብሔር ፡ ዕሩቅ ፡ ነው ፤ ጥበቡ ፡ አይታይምና ። እግዚአብሔር ፡ ቅርብ ፡ ነው ፤ ቶሎ ፡ ይሰማልና ። እግዚአብሔር ፡ መኰንን ፡ ነው ፡ ቶሎ ፡ ይፈርዳልና ። እግዚአብሔር ፡ እንግዳ ፡ ነው ፤ ቶሎ ፡ ወሬ ፡ ይሰማልና ። እግዚአብሔር ፡ ትሑት ፡ ነው ፤ ሰውን ፡ አይንቅምና ። እግዚአብሔር ፡ መሐሪ ፡ ነው ፤ ቶሎ ፡ ይቅር ፡ ይላልና ፡ ሩኅሩኅ ፡ ነው።



እግዚአብሔር ፡ ሐኪም ፡ ነው ፤ ሁሉን ፡ በጥበብ ፡ አድርጓልና ። እግዚአብሔር ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤ ፀሐይን ፡ ጨረቃን ፡ ፈጥሮአልና ። እግዚአብሔር ፡ ክቡር ፡ ነው ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ የርሱ ፡ ናቸውና ።

እግዚአብሔር ፡ ባለጸጋ ፡ ነው ፤ ለሁሉ ፡ ይመግባልና ። እግዚአብሔር ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፤ አይጨበጥምና ። እግዚአብሔር ፡ ግዙፍ ፡ ነው ፤ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ሞልቷልና ። እግዚአብሔር ፡ ብሩህ ፡ ነው ፤ ጨለማ ፡ የለበትምና ። እግዚአብሔር ፡ ኃያል ፡ ነው ፤ የሚቋቋመው ፡ የለምና ።

እግዚአብሔር ፡ እሳት ፡ ነው ፤ እጅግ ፡ ያስፈራልና ። እግዚአብሔር ፡ መክር ፡ ነው ፤ መጻሕፍትን ፡ ሰጥቶናልና ። እግዚአብሔር ፡ አባት ፡ ነው ፤ አሳድጎናልና ። እግዚአብሔር ፡ ወንድም ፡ ነው ፤ ሰው ፡ ሆኖዋልና ። እግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ነው ፤ የሆዱን ፡ ነግሮናልና ።

እግዚአብሔር ፡ አገር ፡ ነው ፤ እንኖርበታለንና ፤ እግዚአብሔር ፡ ማርና ፡ ሱክር ፡ ነው ፤ ይጣፍጣልና ። እግዚአብሔር ፡ ገናና ፡ ነው ፤ የሚያህለው ፡ የለምና ። እግዚአብሔር ፡ ትልቅ ፡ ነው ፤ ስፍራ ፡ አይበቃውምና ። እግዚአብሔር ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፤ በዋና ፡ አይገኝምና ። እግዚአብሔር ፡ ፋሲካ ፡ ነው ፤ ለሁሉ ፡ ታርዷልና ። እግዚአብሔር ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ ነው ። ለሁሉ ፡ ደስታ ፡ ነውና ። እግዚአብሔር ፡ ጨው ፡ ነው ፤ ሁሉን ፡ ያጣፍጣልና ። እግዚአብሔር ፡ ክረምት ፡ ነው ፤ ሁሉን ፡ ያበቅላልና ። እግዚአብሔር ፡ አይጠረጠርም ፡ ሁሉን ፡ ያውቃልና ። እግዚአብሔር ፡ አይዘነጋም ፤ በሁሉ ፡ ድካም ፡ የለበትምና ። እግዚአብሔር ፡ አይሰጋም ፤ የሚሸረው ፡ የለምና ።

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ፡ የሰው ፡ ሎሌ ፡ ነው ፤ በክረምት ፡ ለማብቀል ፤ በበጋ ፡ ለማብሰል ፤ የተዘጋጀ ፡ ነውና ። እግዚአብሔር ፡ እንግዳ ፡ አይደለም ፤ ከጥንት ፡ የነበረ ፡ ነውና ። ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለአብ ፤ ለወልድ ፤ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጥንት ፡ ለነበረ ፤ አሁን ፡ ላለ ፤ ኋላም ፡ ለሚኖር ፡ አሜን ።

ክፍል ፡ ፯ ።

ኢዮብ ፡ መከራ ፡ ቢታገስ ፤ ለራሱ ፡ ብዙ ፡ እጥፍ ፡ ገንዘብ ፡ አገኘ ። ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ያንን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ቢታገስ ፡ ለኛ ፡ ጥቅም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለራሱ ፡ አይደለም ። ሰምሶን ፡ በሰስት ፡ መቶ ፡ ቀበሮ ፡ ጅራት ፡ እሳት ፡ አቆራኝቶ ፡ የፍልስጥኤምን ፡ አዝመራ ፡ አቃጠለ ። ክርስቶስ ፡ ግን ፡ በአሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አቆራኝቶ ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ በፍቅር ፡ እሳት ፡ አቃጠለ ።

የእግዚአብሔር ፡ ልጅስ ፡ እጅግ ፡ ቀላ ፤ ሥጋ ፡ መሰለ ፤ እውራኑም ፡ እያዩ ፤ ደንቆሮዎችም ፡ እየሰሙ ፤ አንካሶችም ፡ እየሮጡ ፡ አደነቁት ።

ክርስቶስ ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ ላይ ፡ ቢለወጥባቸው ፡ ሁሉም ፡ ወደቁ ። ጴጥሮስም ፡ ይወለፍት ፡ ጀመር ፤ ይህ ፡ ባላገር ፡ አምላክን ፡ አይቶት ፡ አያውቅ ፡ ይሆን ፤ አምላክን ፡ አይቶ ፡ እንደዚህ ፡ የፈራ ፡ ሌላ ፡ መከራ ፡ ቢመጣበት ፡ እንዴት ፡ ሊሆን ፡ ነው ።

የፍቅር ፡ ምንጭ ፡ ማነው ፤ ክርስቶስ ፡ ነው ። አምስት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ለተራቡ ፡ ሥጋውን ፡ አብልቶ ፡ ደሙን ፡ አጠጥቷልና ። አይሁድ ፡ ጠማቸውን ፡ አጥርተው ፡ ይጠማሉ ፤ ክርስቲያኖች ፡ ግን ፡ ጠማቸው ፡ የጠራ ፡ አይደለም ፤ እርቡ ፡ የታረደውን ፡ የበግ ፡ ሥጋ ፡ ይበላሉና ።



አይሁድ ፡ ከእንስሳ ፡ እንኳ ፡ ለይተው ፡ ነው ፡ የሚበሉ ፤ ክርስቲያኖች ፡ ግን ፤ ወንድማቸውን ፡ ይበላሉ ።

ዮሐንስ ፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በግ ፡ ቢል ፤ አይሁድ ፡ ላይበሉት ፡ ተሽቀዳድመው ፡ አረዱት ። እነሆ ፡ አይሁድ ፡ ያረዱትን ፡ በግ ፡ አሕዛብ ፡ እየበሉ ፡ ወፈሩ ፤ ቁመታቸውም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደረሰ ። እስራኤል ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ የማንም ፡ መሳቂያ ፡ ሆኑ ።

መጽሐፍ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜስ ፡ አያውቅም ፤ ሰው ፡ ቢሞት ፡ ደስ ፡ አይበልህ ፡ ይላል ። ክርስቶስ ፡ ባይሞት ፡ ለኔ ፡ መንግሥትን ፡ ማን ፡ ይሰጠኝ ፡ ኖሯል ። የርሱ ፡ ሞት ፡ እኔን ፡ ጠቀመኝ ፡ እሰይ ፤ እሰይ ፤ እንኳን ፡ የሞተልኝ ፤ እልል ፤ እልል ፤ እንግዴህማ ፡ ሥጋውንስ ፡ በበላው ፤ ደሙንም ፡ በጠጣው ፡ ምነው ። እኔን ፡ የመሰላችሁ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።

ዳዊት ፡ ይሁዳን ፡ አገሩን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ትሁን ፡ እያለ ፡ ምን ፡ ያራግመዋል ፤ እርሱ ፡ ካልበላሁለት ፡ ብሎ ፡ ነውን ፤ እንደ ፡ ይሁዳ ፡ ያለ ፡ መልካም ፡ ነጋዴ ፡ የለም ፤ የዘለዓለሙን ፡ ምግብ ፡ በ፴ ፡ ብር ፡ ሸጠልን ።

የግዚአብሔር ፡ ልጅስ ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ በረታ ፡ ከአንዲት ፡ ሴት ፡ ሥጋ ፡ ነጥቆ ፡ ወስዶ ፡ በሰው ፡ መካከል ፡ በቀራንዮ ፡ ሰቀለው ፤ ወይ ፡ አለማፈር ።

እግዚአብሔር ፡ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፤ ከሙሴ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ነቢያት ፡ ድረስ ፡ ጮኸ ፤ ጮኸ ፤ የሚሰማውም ፡ ታጣ ፤ ቃሉም ፡ ታሠረ ፤ እንግዴህ ፡ በምኑ ፡ ይነገራችሁ ።

ክፍል ፡ ፰ ።

አብ ፡ እሳት ፤ ወልድ ፡ እሳት ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሳት ፤ ስሙ ፡ ሰስት ፡ ቢሆን ፡ ኪሩቤል ፡ ይጨንቁ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ምን ፡

www.ethiopianorthodox.org

እዳዬ ፤ መቶውንም ፡ አንድ ፡ እሳት ፡ ነው ፤ በሥጋዬ ፡ በቅልዬ ፡ ተሸክሜዋለሁ ። ኪሩቤልማ ፡ በስም ፡ እንስሶች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ጥቂት ፡ እንኳ ፡ ሥጋ ፡ የላቸውም ። ይህን ፡ የማይጠፋ ፡ እሳት ፡ እንዴት ፡ ይችሉታል ።

አሪት ፡ በጋ ፡ ናት ፤ አድርቃ ፡ አንድዳለችና ። ወንጌል ፡ ክረምት ፡ ናት ፤ ሁሉን ፡ አብቅላለችና ። አሪት ፡ እሬት ፡ ናት ፡ ሁሉን ፡ አምርራለችና ። ወንጌል ፡ ግን ፡ ማር ፡ ናት ፡ ሁሉን ፡ አጣፍጣለችና ።

በንጹሕ ፡ ሰው ፡ ልብ ፡ ምድጃ ፡ እብ ፡ ይጣዳል ፤ ወልድ ፡ ይፈላል ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይገነፍላል ። አሪት ፡ ጨረቃ ፡ ናት ፤ ወንጌል ፡ ግን ፡ ፀሐይ ፡ ናት ፤ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ሞቃ ፡ ታበራለችና ። አሪት ፡ በትሀ ፡ ናት ፡ ወንጌል ፡ ግን ፡ ጥሩ ፡ ጠጅ ፡ ናት ፤ በልክ ፡ ለሚጠጣት ፡ ሰው ፡ ጤና ፡ ሕይወት ፡ ትሰጣለችና ።

አሪት ፡ አበባ ፡ ናት ፤ ወንጌል ፡ ግን ፡ ፍሬ ፡ ናት ፡ ሁሉን ፡ ታጠግባለችና ። ምን ፡ እበላ ፤ ምን ፡ እጠጣ ፤ ምን ፡ እለብስ ፡ እያለ ፡ ሰው ፡ ለምን ፡ ያስባል ። አርባ ፡ ዓመት ፡ ለእስራኤል ፡ መናን ፡ ያበላ ፤ ለሰማዮ ፡ ደመናን ፡ የከለለ ፡ ለኤሊ ፡ ድንጋይን ፡ ያለበሰ ፡ አምላክ ፡ ይነሣዋልን ።

አሪት ፡ ገጠር ፡ ናት ፡ ወንጌል ፡ ግን ፡ ከተማ ፡ ናት ፡ ሁሉ ፡ ይገኝባታልና ። ወርቅ ፡ ከሥሩ ፡ እየወፈረ ፡ ከጫፉ ፡ እንዲሰፋ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ እንደዚያ ፡ ናት ።

በሁለት ፡ አህያ ፡ ተጭኖ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የገባ ፡ መድኃኒት ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ አዳነ ።

ሙሴ ፡ አሥር ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አስፈጀ ። ምነው ፡ ባልተናገረ ፡ የማይችሉውን ፡ ነገር ፤ ሙሴ ፡ ባጠፋ ፤ ክርስቶስን ፡ ሥጋ ፡ ጥሬውን ፡ ይበሉታል ። ምነው ፡ ይሆን ፡ ፊት ፡ ከሙሴ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ይሆን ።



እግዚአብሔርስ ፡ ሰው ፡ ባጠፋ ፤ በሥሩ ፡ አመከኝቶ ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ ቢያስገድለው ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ተጠቀመ ። አዳም ፡ እንደኛ ፡ እንዳንዱ ፡ ሆነ ፡ ያለውን ፡ እፈጽም ፡ ብሎ ፡ ነውን ።

ክርስቶስስ ፡ ከሙሴ ፡ ጋር ፡ ቀድሞ ፡ ምክር ፡ ያለው ፡ መሰለ ፤ ሥጋውን ፡ ሲበሉት ፡ ዝም ፡ ይላልና ፤ እነዚያስ ፡ አራቱ ፡ ዙፋን ፡ ቤቶች ፡ ዓይን ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤ አያዩምን ፡ ጌታቸው ፡ ባህያ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ያህል ፡ ከተማ ፡ ሲገባ ፡ እያዩ ፡ ዝም ፡ ይላሉሳ ፡ እንስሶች ፡ ናቸው ።

መስቀል ፡ አይሁድን ፡ አጠፋ ፤ ክርስቲያንን ፡ ግን ፡ ጠቀመ ፡ አዳነ ፤ ንጉሡ ፡ ቈስጠንጢኖስም ፡ በመስቀል ፡ ታፍሯል ፤ ለካ ፡ መስቀል ፡ መልካም ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ያስኮነናል ፡ ብዬ ።

አይሁድ ፡ ክርስቶስን ፡ ያጣሮች ፡ ያመንዝሮች ፡ ወዳጅ ፡ ብለው ፡ የአሙት ፡ ለካ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ በአንድ ፡ ብርሌ ፡ ሽቱ ፡ ያመንዝራይቱን ፡ ኃጢአት ፡ ፋቀላት ። በቀኙ ፡ የተሰቀለውም ፡ ቀማኛ ፡ አቤቱ ፤ በመንግሥትህ ፡ አስበኝ ፡ ብሎ ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ ቢናገረው ፤ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ገነት ፡ አገባው ።

አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ በገነት ፡ የሠረቁትን ፡ መልሶ ፡ አገባቸው ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጌታ ፡ መቶም ፡ አይገኝ ፤ ምነው ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ ቢሾም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ወዳጅ ፤ የሰውን ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ተሸክሞ ፡ የማይከብደው ፤ ኃጢአተኛ ፡ የሆንህ ፡ ወዲህ ፡ ና ። ኃጢአትህን ፡ የሚሸከም ፡ ክርስቶስ ፡ አለልህ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ገበያ ፡ የምትነግዱ ፡ የዓለሙን ፡ የኃጢአት ፡ ትብትብ ፡ የሚሸክም ፡ ሰው ፡ በቀራንዮ ፡ ቆሞላችኋል ፤ የናንተን ፡ ትብትብ ፡ የሚሸከም ፡ ሌላ ፡ የለም ፤ ሌላ ፡ ተሸካሚ ፡ ለምን ፡ ትፈልጋላችሁ ። ሌላው ፡ ግን ፡ ገንዘባችሁን ፡ ወስዶ ፡ ሸክማችሁን ፡ ያከብድባችኋልና ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፡ ፱ ።

መላእክትስ ፡ ጠጅና ፡ ሥጋ ፡ አይወዱም ፡ ይሆን ፤ ለሰው ፡ ልጆች ፡ በሥጋ ፡ ሲያደላ ፡ አይተው ፡ ይሆን ፤ ምነው ፡ ጌታቸው ፡ ሲሰቀል ፡ ዝም ፡ አሉ ፤ ጌታቸው ፡ ሲሰቀል ፡ ከቶ ፡ ወዴት ፡ ሸሹ ፤ ምናልባት ፡ እንደርሱ ፡ እንሞታለን ፡ ብለው ፡ ይሆን ፤ መንጋ ፡ ፈሪ ፡ በሰማይ ፡ ተሰብስበ። ሰይፍን ፡ አስረ ዝሞ ፡ አስረገዘሞ ፡ ቢቆሙት ፡ ከልመተበት ፡ ምን ፡ ይሆናል ፤ የፈሪ ፡ በትሩ ፡ አሥር ፡ ነው ።

ይልቅስ ፡ ሥጋ ፡ የበላው ፡ ጠጅ ፡ የጠጣው ፡ ጴጥሮስ ፡ ይሻላል ፤ የማልኩስን ፡ ጆሮ ፡ በሰይፍ ፡ የመነጠረው ።

እንግዴህ ፡ መላእክት ፡ ከሥጋና ፡ ከጠጅ ፡ ይከልከሉ ፡ ጌታቸውን ፡ ብቻውን ፡ አስደብድበውታልና ።

ይልቁንስ ፡ ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፡ ተሽልሞ ፡ መኖር ፡ ይገባቸዋል ፤ የጌታቸውን ፡ ራቁትነት ፡ ቢያዩ ፡ ብርሃናቸውን ፡ ሰውረዋልና ፤ ከዋክብትም ፡ ረግፈዋልና ፡ ክብር ፡ ይገባቸዋል ። ሀያ ፡ አራቱ ፡ ቄሶችስ ፡ ወዴት ፡ ሄደው ፡ ነው ፤ የሱፍና ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እያሉ ፡ የቀበሩት ፡ የጦር ፡ ቀን ፡ ያልሆነ ፡ ለሌሊ ፡ ለመቸ ፡ ነው ። መንጋ ፡ ቀጥቃጣ ፡ ሞት ፡ ፈሪ ፤ እንዲያውም ፡ አረማቸውን ፡ ሁለቱ ፡ ይመሰዱባቸው ።

ምድርስ ፡ የእግሩ ፡ ረጊማ ፡ አልነበረችምን ፤ እንዴት ፡ መቃብር ፡ ሆነችው ። ወይ ፡ ጊዜ ፤ ለካ ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ለሁሉ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፡ ያለው ፡ እውነት ፡ ነው ።

መቃብርስ ፡ አሁን ፡ ስም ፡ ሆነባት ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ሆናት ፤ እንደ ፡ አልዓዛር ፡ እንኳ ፡ ያራት ፡ ቀን ፡ አራት ፡ አልሆናት ። ማርያም ፡ መግደላዊትም ፡ ለካ ፡ የዋህ ፡ ናት ፤ ሽቱ ፡ አዘጋጅታ ፡ አሬሳ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ልትቀባ ፡ የሄደች ።



ለአንተ ፡ ለማርታ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ትንሣኤ ፡ ሕይወት ፡ ሲል ፡ አልሰማችምን ። ወይም ፡ ተንሥቼ ፡ ገሊላ ፡ እቀድማችኋለሁ ፡ ሲል ፡ አልሰማችምን ።

የዳዊት ፡ ቤት ፡ ግልግል ፡ አንበሳ ፡ በሰስት ፡ ቀን ፡ ተነሣ ፤ ሰላሣ ፡ ብር ፡ ለይሁዳ ፡ ደስታው ፡ ነው ፤ ለክርስቶስ ፡ ግን ፡ ጭንቀቱ ፡ ሞቱ ፡ ነው ። ለክርስቲያን ፡ ግን ፡ መልካም ፡ ገበያ ፡ ጥቅማችን ፡ ነው ።

ሙሴ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አጽፎ ፡ በሣጥን ፡ ከተተ ። የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ ይኖርን ፡ ብሎ ፡ ነው ፤ ወይስ ፡ ወንጌልን ፡ ባይሰማ ፡ ነው ፤ በሣጥን ፡ አትሰብስቡ ፡ ማለቱ ። እነሆ ፡ የናልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ ከነሣጥኑ ፡ ወሰዱለት ። እኛስ ፡ በሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በላነው ። የእኛ ፡ ሣጥን ፡ ልባችን ፡ ሆዳችን ፡ ነውና ፡ ጳውሎስም ፡ ሣጥኑ ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ፡ ብሎናልና ።

አይሁድ ፡ ጅሎች ፡ ናቸው ፤ ክርስቶስ ፡ ከሰማይ ፡ ወረድሁ ፡ ቢላቸው ፡ ከእንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቀሉት ፤ ያውም ፡ እንጨት ፡ ከነእኮቴው ፡ መሰላል ፡ የሰማይ ፡ መውጫ ፡ ሆነ ።

እግዚአብሔር ፡ ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ በግ ፡ ሰደደ ፤ አምስት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ለተራበ ። እናንተ ፡ ምእመናን ፡ ሥጋውን ፡ ብሉታችሁ ፤ ምናልባት ፡ ባይበቃችሁ ፡ ደሙን ፡ ጠጡት ። አሬት ፡ ደም ፡ አትጠጡ እያለች ፡ ረሀብ ፡ ትሞታላችሁን ፤ ዛሬ ፡ ጠጥታችሁት ፡ ከሞት ፡ ዳኑና ፡ በኋላ ፡ ንስሐ ፡ ትገባላችሁ ። እናንተ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነጋዴዎች ፡ ከዚህ ፡ ከአንድ ፡ በግ ፡ ሥጋ ፡ ተቀራምታችሁ ፡ ምነው ፡ ስንቃችሁን ፡ ብትይዙ ።

---

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፡ ፱ ።

መላእክትስ ፡ ጠጅና ፡ ሥጋ ፡ አይጠጡም ፡ ይሆን ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ በሥጋ ፡ ሲያደላ ፡ አይተው ፡ ይሆን ፡ ምነው ፡ ጌታቸው ፡ ሲሰቀል ፡ ዝም ፡ አሉ ፡ ጌታቸው ፡ ሲሰቀል ፡ ከቶ ፡ ወዴት ፡ ሸሹ ፤ ምናልባት ፡ እንደርሱ ፡ እንሞታለን ፡ ብለው ፡ ይሆን ፡ መንጋ ፡ ፈሪ ፡ በሰማይ ፡ ተሰብስበ። ሰይፍን ፡ አስረዝሞ ፡ አስረዝሞ ፡ ቢቆሙት ፡ ካልመቱበት ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ የፈሪ ፡ በትሩ ፡ አሥር ፡ ነው ።

ይልቅስ ፡ ሥጋ ፡ የበላው ፡ ጠጅ ፡ የጠጣው ፡ ጴጥሮስ ፡ ይሻላል ፤ የማልኩስን ፡ ጆሮ ፡ በሰይፉ ፡ የመነጠረው ።

እንግዲህ ፡ መላእክት ፡ ከሥጋና ፡ ከጠጅ ፡ ይከለከሉ ፡ ጌታቸውን ፡ ብቻውን ፡ አስደብድበውታልና ።

ይልቁንስ ፡ ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፡ ተሽለዋል ፡ መሬር ፡ ይገባቸዋል ፤ የጌታቸውን ፡ ራቁትንት ፡ ቢያዩ ፡ ብርሃናቸውን ፡ ሰውረዋልና ፤ ከዋክብትም ፡ ረግፈዋልና ፡ ክብር ፡ ይገባቸዋል ። ሆያ ፡ አራቱ ፡ ቁሶችስ ፡ ወዴት ፡ ሄደው ፡ ነው ፡ ዮሴፍና ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እያሉ ፡ የቀበሩት ፡ የጦር ፡ ቀን ፡ ያልሆነ ፡ ሉሌ ፡ ለመቸ ፡ ነው ። መንጋ ፡ ቀጥቃጣ ፡ ሞት ፡ ፈሪ ፤ እንዲያውም ፡ አረማቸውን ፡ ሁለቱ ፡ ይውሰዱባቸው ።

ምድርስ ፡ የእግሩ ፡ ጫማ ፡ አልነበረችምን ፡ እንደት ፡ መቃብር ፡ ሆነችው ። ወይ ፡ ጊዜ ፤ ለሽ ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ለሁሉ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፡ ያለው ፡ እውነት ፡ ነው ።

መቃብርስ፡አሁን ፡ ስም፡ሆነባት ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ሆናት ፤ እንደ ፡ አልዓዛር ፡ እንኳ ፡ ያራት ፡ ቀን ፡ እራት ፡ አልሆናት ። ማርያም ፡ መግደላዊትም ፡ ለካ ፡ የዋህ ፡ ናት ፤ ሽቱ ፡ አዘጋጅታ ፡ እሬሳ ፡ ነው ፡ ብላ፡ልትቀባ ፡ የሄደች ።



ለእኅቱ ፡ ለማርታ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ትንሣኤ ፡ ሕይወት ፡ ሲል ፡ አልሰማችምን ። ወይም ፡ ተነሥቼ ፡ ገሊላ ፡ እቀድማችኋለሁ ፡ ሲል ፡ አልሰማችምን ።

የዳዊት ፡ ቤት ፡ ግልገል ፡ አንበሳ፡በሶስት፡ቀን፡ተነሣ ፤ ሰላሳ ፡ ብር ፡ ለይሁዳ ፡ ደስታው ፡ ነው ፤ ለክርስቶስ ፡ ግን ፡ ጉንቁቱ ፡ ሞቱ ፡ ነው ። ለክርስቲያን ፡ ግን ፡ መልካም ፡ ገበያ ፡ ጥቅማችን ፡ ነው ።

ሙሴ፡የእግዚአብሔርን ፡ ቃል፡አጽፎ ፡ በማጥን ፡ ከተተ ። የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ ይዋርን ፡ ብሉ ፡ ነው ፤ ወይስ ፡ ወንጌልን ፡ በይሰማ ፡ ነው ፤ በማጥን ፡ አትሰብስቡ ፡ ማለቱ ። እነሆ ፡ የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ ከነማጥኑ ፡ ወሰዱለት ። እኛስ ፡ በሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በላነው ። የእኛ ፡ ማጥን ፡ ልባችን ፡ ሆዳችን ፡ ነውና ፡ ጳውሎስም ፡ ማጥኑ ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ፡ ብሎናልና ።

አይሁድ፡ጅሎች፡ናቸው፡ክርስቶስ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደሁ ፡ ቢላቸው ፡ ከእንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቀሉት ፤ ያውም ፡ እንጨት ፡ ከነእኾቴው ፡ መሰላል ፡ የሰማይ ፡ መውጫ ፡ ሆነ ።

እግዚአብሔር ፡ ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ በግ ፡ ሰደደ ፤ አምስት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ለተራቡ ። እናንተ ፡ ምእመናን ፡ ሥጋውን ፡ በልታችሁ ፤ ምናልባት ፡ ባይበቃችሁ ፡ ደሙን ፡ ጠጡት ። አሪት ፡ ደም ፡ አትጠጡ እያለች ፡ ረሀብ ፡ ትሞታላችሁን ፤ ዛሬ ፡ ጠጥታችሁት ፡ ከሞት ፡ ዳኑና ፡ በኋላ ፡ ንስሐ ፡ ትገባላችሁ ። እናንተ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነጋዴዎች ፡ ከዚህ ፡ ከአንድ ፡ በግ ፡ ሥጋ ፡ ተቀራምታችሁ ፡ ምነው ፡ ስንቃችሁን ፡ ብትይዙ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፡ ፲ ።

እናንተ ፡ የአዳም ፡ ልጆች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የላችሁ ፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በግ ፡ ወሀችሁን ፡ ሊጠጣ ፡ መጥቷልና ፡ በጣም ፡ ደሙን ፡ ምጠጡት ፡ ጤና ፡ ይሆናችኋልና ፡ አትልቀቁት ።

ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ዓሣ ፡ ቤት ፡ ልሔም ፡ የተገኘ ። በብርብራ ፡ የዓለም ፡ ኃጢአት ፡ የሰከረ ፡ ተይዞ ፡ በቀራንዮ ፡ በሰቀል ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ አጠገበ ።

ሰይጣን ፡ በይሁዳ ፡ ልብ ፡ ገብቶ ፡ ክርስቶስን ፡ ቢያስገድል ፡ ምን ፡ ተጠቀመ ። ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ተዘረፈ ፡ እንጂ ፡ ደባ ፡ ራሱን ፤ ስለት ፡ ድጉሱን ፡ እንደሚሉት ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ እጅግ ፡ ተጎዳ ፡ እንጂ ። ማን ፡ ተገምዳለት ፡ ከገነት ፡ የዘረፈው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ተመልሶ ፡ ገነት ፡ ገባ ።

ክርስቶስስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሞቶ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ማነን ፡ ይሰልላል ። ሰማይንና ፡ ምድርንስ ፡ መውደዱ ፡ ምንድር ፡ ነው ።

ደግሞስ ፡ እሥሩ ፡ ፍቱ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ መውጣቱ ፤ ይህንስ ፡ ያህል ፡ ሥልጣን ፡ ለሰው ፡ መስጠቱ ፤ በአሥር ፡ ቀንስ ፡ ጰራቅሊጦስን ፡ ልኮ ፡ በሰናኦር ፡ የተለዋወጠውን ፡ ቋንቋ ፡ ለሐዋርያት ፡ ገልጦ ፡ ማናገሩ ፡ ምድርን ፡ መውደዱ ፡ አይደለምን ።

ይህንን ፡ ሁሉ ፡ እያደረገ ፡ መንግሥት ፡ ማስፋቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ። ተመልሶ ፡ በልታወቀ ፡ ቀን ፡ ለመምጣት ፡ አይደለምን ፤ እናንተ ፡ ወንድሞቼ ፡ ምዕመናን ፡ የወንጌልን ፡ ሰላም ፡ ጥሩር ፡ አድርጋችሁ ፤ ሃይማኖትን ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡ ይዛችሁ ፡ ተሰልፋችሁ ፡ ቆዩት ። ያለዚያ ፡ እሳቱን ፡ ለብሶ ፡ እሳቱን ፡ ጉርሶ ፡ ይመጣላችኋል ፤ በእሳቱ ፡ ላቦቱም ፡ ያጠፋችኋል ።



## ክፍል ፡ ፲፩ ።

ክርስቶስ ፡ አዳራሽ ፡ የተገኘ ፡ ለት ፡ ምን ፡ ብለን ፡ እንፈክራለን ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ተነሡ ፤ የሃይማኖትን ፡ ጥሩር ፡ ልበሱ ፤ የሰላምን ፡ ሰይፍ ፡ ታጠቁ ፤ ጽድቅን ፡ እናድናት ፤ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ዳር ፡ ግብታለችና ፤ ቆንጆዪቱ ፤ ቀንጠፉ ፡ ጠጅ ፡ ሥጋው ፡ ጌጡ ፤ ገመሮ ፡ ብሩ ፤ ኩራቱ ፡ ቀጋ ፤ ሆነው ፡ ሰውረዋታልና ፡ እየጣስናቸው ፡ እንሂድ ፡ ጽድቅን ፡ እናገኛታለንና ። እሷን ፡ ይዘን ፡ ባዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ሳናፍር ፡ እንድንፈክር ።

ኢየሩሳሌም ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ትኃታላችሁ ፤ ነቢያትን ፡ ሁሉ ፡ የገደለች ፤ በመጨረሻውም ፡ ጌታዋን ፡ የሰቀለች ፡ አይደለችምን ፤ ትሠርቃለች ፤ ተቀጥፋለች ፤ ታመነዝራለች ፡ ከቶ ፡ ምንድር ፡ ናት ። ለከ ፡ አንተ ፡ አታውቃትምን ፡ ባሪያ ፡ እኮ ፡ ናት ፡ አሉ ፤ እንደዚህ ፡ እመቤት ፡ መስላ ፡ የምትቀልጥብን ።

አሁን ፡ ምን ፡ ይሆናኝ ፡ ብላ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ኩራት ፡ እመቤት ፡ እያለቻት ፤ አንድስ ፡ መልክ ፡ ቢስ ፡ አፈር ፡ መሳይ ፤ አሁን ፡ ባርነቷ ፡ አልታወቀብኝም ፡ ብላ ፡ ነውን ፤ እነሆ ፡ እመቤቷ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊቱም ፡ ያደረገችውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሰምታለች ።

አሁን ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ኢያበራች ፡ የመጣች ፡ ለት ፡ ድምጿ ፡ ይጠፋል ። ሙሆ ፡ ለመሆን ፤ ለመቅለጥ ፡ ብላ ፡ ነው ።

ከቶ ፡ ባሪያ ፡ ከባርነቱ ፡ አይወጣም ። እንድትጠፋ ፡ ባታውቀውን ፡ ይሆን ።

የችስ ፡ እመቤቷ ፡ ምን ፡ እንደዚህ ፡ አሰለቻት ፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሽፋት ፡ እየሰማች ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ አፈጽም ፡ ብላ ፡ ነው ፡ መቀጣቷ ።

www.ethiopianorthodox.org

ባይሆን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መጥታ ፡ በሪያዋን ፡ ቀጥታ ፡ ከኛም ፡ ኃሪ ፡ ተገናኝታ ፡ ጌጧን ፡ ውበቱዋን ፡ ሁሉ ፡ ዓይተነው ፤ ተጫዋውተን ፡ ጠግበናት ፡ ተሰነባብተን ፡ ተመልሳ ፡ አትሄድምን ።

እኛ ፡ ልጆቿ ፡ ሁልጊዜ ፡ ትምጣ ፡ ትምጣ ፡ እያልን ፡ ጧትና ፡ ማታ ፡ አሁን ፡ ብንናፍቃት ፡ ብንጐመጀላት ፡ ምን ፡ ተጠቀመች ፡ እናሳዝናትም ፡ ይሆን ፤ እንደዚህ ፡ መጥናቷና ፡ መጨከኗስ ፡ ወልዳ ፡ ባታውቅ ፡ ይሆን ።

ደግሞስ ፡ የመጣሁ ፡ እንደሆን ፡ ከድተው ፡ ይይዙኛል ፡ አይሰዱኝም ፡ ብላ ፡ ፈርታ ፡ ይሆን ፤ የፈራች ፡ እንደሆን ፡ ዋስ ፡ እንጥራላት ፡ ዋሱንም ፡ ብትጠላ ፡ ቃምለን ፤ ቃስገዝተን ፤ አይተናት ፡ ተጫዋውተን ፡ ተመልሳ ፡ እንድትሄድ ።

ወንድሞቿ ፡ ምእመናን ፡ ሰው ፡ አይስማ ፡ ምለን ፡ ተገዝተን ፡ እናታላት ፤ እናምጣትም ፡ በመጣችልን ፡ ግን ፡ ከጡቷ ፡ ስር ፡ ተሸጉጠን ፡ ተሸጉጠን ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ አለመስደድ ፡ ነው ።

ከዚያ ፡ ስፍራ ፡ መሐላና ፡ ግዝት ፡ አይደርስምና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እርሷን ፡ አስቀርተን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቅልናል ፡ ምን ፡ ያገኘን ፡ ብላችሁ ።

ጴጥሮስና ፡ ጳውሎስ ፡ መድኃኒት ፡ ያላቸው ፡ ይመስለኛል ። የሞተውም ፡ የታመመውም ፡ ይነሣላቸዋልና ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ግርማ ፡ ክታብ ፡ ሰፍተው ፡ ይዘው ፡ ይሆን ፤ ኧረ ፡ ገና ፡ ክታባቸውንማ ፡ ደኅና ፡ እንደሆነ ፡ እናውቀው ፡ የለምን ፤ ጴጥሮስስ ፡ ያለሁለት ፡ ክታብ ። ጳውሎስስ ፡ ያለአሥራ ፡ አራት ፡ ክታብ ፡ ምን ፡ ክታብ ፡ አላቸው ፤ እንኳን ፡ መድኃኒቱንስ ፡ በልተውታል ፡ በሆዳቸው ፡ ነው ፡ አሉ ።

ጉጉት ፡ አሞራ ፡ ናት ፤ ፊቷም ፡ እንደ ፡ ድመት ፡ ነው ፤ ድምጧም ፡ የከፋ ፡ ነው ። መናፍቃንም ፡ መልካቸው ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ሥራቸው ፡ ግን ፡ የሰይጣን ፡ ነው ።



እንድርማሚት ፡ ዖፈ ፡ ያሬድ ፡ የምትባል ፡ መልኳ ፡ ያማረ ፡ ነው ፤ ድምጧም ፡ የጣፈጠ ፡ ነው ። እንደዚች ፡ ቤት ፡ ክርስቲያንም ፡ በፍቅር ፡ ያጌጠች ፤ ያማረች ፡ የተሸለመች ፡ ናት ። በርኅራኄም ፡ የተዋበች ፡ ናት ፤ ቃሏም ፡ ወንጌል ፡ ነውና ።

ጉንዳን ፡ በደረሰበት ፡ እንደሚቆነጥጥ ፤ መናፍቃንም ፡ በደረሱበት ፡ ጤና ፡ የላቸውም ።

ሰማይ ፡ ከዚያ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ አንዣበብን ፡ የሚኖር ፡ ከቶ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ቀን ፡ ፀሐይን ፤ ሌሊት ፡ ጨረቃንና ፡ ከዋክብትን ፡ ተሸልሞ ፡ ዘወትር ፡ እኔን ፡ እኔን ፡ እዩኝ ፤ እዩኝ ፡ እያለ ፡ ያደክመናል ፡ ምነው ፤ የናቀን ፡ ድሆች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ነውን ፤ ረሳው ፡ መሰለኝ ፡ የወትሮው ፡ እንዳይመስለው ፤ በላዩ ፡ የተቀመጠው ፡ ወንድማችን ፡ ነውና ። እርሱም ፡ ተመልሶ ፡ አሁን ፡ ይመጣል ፤ እንደዚህ ፡ የከረ ፡ እንደሰም ፡ ሊመቅለጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፊቱን ፡ እንዴት ፡ ያየው ፡ ይሆን ፡ ኩራቱም ፡ ምድር ፡ አስለቅቆታል ፤ ምን ፡ ይሆናል ፡ እንደሚያልፍ ፡ አያውቅምን ።

ምድርንስ ፡ ተገርአቸው ፡ ቢላት ፡ ገደልና ፡ ዱር ፡ ባሕርም ፡ እየሆነች ፡ ለምን ፡ ታውከናለች ።

ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ አስተምራት ፡ ብሎ ፡ ቢሰድላት ፡ ልጁን ፡ አስደብድበ ፡ አስገደለችውና ፡ ዋጠችው ፡ ጤናም ፡ አልሆናት ፤ በዋጠችው ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ አስታወከች ።

ዳታንንና ፡ አቤሮንን ፡ መስዕት ፡ ሲታላምጥ ፡ ዋጠችውና ፡ ካስታወከች ፡ በኋላ ፤ እነሆ ፡ ከሰማይ ፡ በባቱ ፡ ቀኝ ፡ ተቀምጧል ። ወንድማችን ፡ መሆኑን ፡ አታውቅምን ፤ የታዘዘችውን ፡ ትታ ፡ ለሆዷ ፡ እውጥ ፡ እውጥ ፡ ማለት ፡ ምንድር ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

እስቲ ፡ እንደምን፡ትሆናለች ፤ ያ፡ወንድማችን ፡ የመጣ፡ ለት ፡ እንደ ፡ ሰም ፡ ለመቅለጥ ፡ ብላ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የሚያልፍ ፡ ኩራት ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ይሆናል ፤ እንዲያው ፡ ቀለት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ብርሃን ፡ ከፀሐይ፡ጋር ፡ ምን ፡ ያለማምጠዋል ፡ እርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ተፈጥሮ ፡ የለምን ፤ ነገር ፡ ግን ፤ ልዩምስስህ ፡ እያለው ፡ ሆዱን ፡ ይከፋዋል ፡ እንጂ ፡ ዘመድ ፡ ናቸው ።

ብርሃን ፡ ለእኛ ፡ ዘመዳችን ፡ ነው ። ከፀሐይ፡ቀድሞ ፡ ስናየው ፡ ደስ ፡ ይለናልና ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ፩ ክፉ ፡ አለበት ፤ ጨለማ ፡ ሲመጣ ፡ ትቶን ፡ ይሸሻል ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከቶ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ክዳት ፡ ያለው ፡ አይታጣም ። በጨለማ ፡ ጊዜ ፡ ጨረቃና ፡ ከዋክብት ፡ ባይኖሩ ፡ ጅብ ፡ በበላን ፡ ነበር ።

ወሀን ፡ አንተ ፡ በሬ ፡ ብለው ፡ እጅግ ፡ ክፉው ፤ እንግዴህስ ፡ ይወቀው ፡ ከቶም ፡ አህያ ፡ ነው ። የሁሉን ፡ እድፍና ፡ ጉድፍ ፡ ተጭኖ ፡ የሚሄድ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ልግመኛ ነው ። ዓይኑ ፡ ሲያይ ፡ ቢጭኑበት ፡ መርፌ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ይጥለዋል ።

በመርከብ ፡ እድርጎ ፡ ሳያይ ፡ ቢጭኑበት ፡ ግን ፡ ፩ሚሊዮን ፡ የሚሆን ፡ መድፍም ፡ አይከብደው ።

ይህም ፡ ተንኮሉና ፡ ልግሙ ፡ አቅጥኖት ፡ ይኖራል ። ሁብቱም ፡ ወደታች ፡ ከመፍሰስ ፡ በቀር ፡ ወደላይ ፡ መውጣት ፡ የለውም ። ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በጉንጩ ፡ እንደያዘው ፡ አያውቅምን ።

እሳትም ፡ ብረትን ፡ ሠርቶ ፤ ጋግሮ ፡ ቀቅሎ ፡ አብስሎ ፡ ሲያበላ ፡ ደግ ፡ ያደርጋል ፤ ሲቀርቡት ፡ ግን ፡ ይፈጃል ፡ ለእኛም ፡ አይገዛ ። ስለዚህ ፡ እንዳይሞት ፡ እንዳይድን ፡ አድርገን ፡ ብናኖረው ፡ ይሻላል ።

ወሀማ ፡ ባይኖርበት ፡ ይቻላልን ። እርሱን ፡ እንኳ ፡ መኪታ ፡

www.ethiopianorthodox.org



አየሰጠ ፡ ሲያነደው ፤ ሲያንፍረው ፤ ሲያጤሰው ፤ መርከብና ፡ ሠረገላ ፡ ሲያስጎትተው ፤ ባቡር ፡ ሲያስነዳው ፤ ሲያስወቅጠው ፡ ሲያስፈጨው ፡ ይኖራል ።

ወሀም ፡ በክረምት ፡ በክረምት ፡ ዘመዳችንን ፡ ይወስዳል ፡ በበጋ ፡ ደግሞ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ከሆዳችን ፡ ስናገባው ፡ የሰውነታችንን ፡ ልክ ፡ ይመረምርና ፡ ይከራል ።

እንዲያውስ ፡ ጠጅ ፡ በጥባጭ ፡ አይደለምን ፤ ጌሾና ፡ ጠጆ ፡ ይቆራኙት ።

ነገር ፡ ግን ፡ ጨርሱን ፡ እንጥላው ። እንዶድ ፡ እደሚቀላቀል ፡ ጌታችንም ፡ መንፈሱን ፡ በውሀ ፡ ቀላቅሎ ፡ አጥቦናልና ።

ፀሐይ ፡ ምንም ፡ ዘመዷ ፡ ብዙ ፡ ሆኖ ፡ ለቆላ ፡ ከምጣጣ ፡ ብትሆን ፡ ለደጋ ፡ በተሀ ፡ ናት ። ቆላ ፡ ምን ፡ ባደረገ ፡ ከመጠጠችበት ፡ ይሆን ። ቢርቃት ፡ ቢሸሻት ።

ደጋማ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ቀርቦ ፡ ይለማመጣታል ፡ ኧረ ፡ ገና ፤ ዘወትር ፡ በረዶ ፡ ሲፈላባት ፡ እያያት ፡ ዝም ፡ ትለው ፡ የለችምን ፤ አይደለም ፡ ስታከርፈው ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ባታከርፈውስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወጥታ ፡ ታቀልጥለት ፡ ነበር ።

ጨረቃና ፡ ከዋክብትስ ፡ መሞቅ ፡ የለ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መቀዝቀዝ ፡ ምንድር፡ነው ። ሰማይ ፡ የለም ፡ ይሆን ፤ ተሰብስበው ፡ ፀሐይን፡የማይዘርፏት፤መንጋ፡ፈሪ ፡ በሰማይ፡ተሰብስቦ።

ደመናም፡የታዘዘው፡ዝናም፡ሊያዘንም፡ታዘዘ፡እንጂ፡እንዲያው ፡ በድንገት ፡ እየመጣ፡የሚያፍነን፡ምን፡ባልነው ፡ ነው።

ነፋስስ ፡ እኛን ፡ ለመግደል ፡ ነው ፡ የታዘዘ ። አሁን ፡ ግንብ ፡ ሠርተን ፡ መውጫ ፡ መተንፈሻ ፡ በሳጣነው ።

ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለአብ ፤ ለወልድ ፤ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ አንድ፡አምላክ፤ቀድሞ፡የነበረ ፤አሁንም፡ያለ ፤ ኋላም ፡ የሚኖር ፤ አስጀምሮ፡ላስጨረሰን፡ክብር ፡ ይግባው ፡ ለዘለዓለም፡አሜን ።